በኢትዮጵያፌዴራላዊዲሞክራሲያዊሪፐብሊክ
የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር
የ2009በጀትዓመትሂሳብኦዲትሪፖርት

የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር የተመደበለትን የመደበኛና የካፒታል ሂሳብ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል::

የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ያቀረባቸው የሂሳብ መግለጫዎች፣መዛግብት፣ደጋፊ ማስረጃዎች፣እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው:: ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር የሂሳብ መግለጫዎች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል::

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድርሂሳብሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብሚዛንሙከራ፣

<u>ለኦዲትአስተያየቱመሠረትየሆኑትጉዳዮች፣</u>

የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር የሂሳብ መግለጫዎች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረትየ ተዘጋጁ እና የተሰበሰበውገቢ፣የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ደንብ ናመመሪያን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

<u>የወጪ ሂሳብ፣</u>

1. በሕንፃ የኪራይ ውል ስለዋጋ ጭማሪ በውሉ በግልፅ ባልተካተተ ያለአግባብ በየዓመቱ የ15% የዋጋ ጭማሪ በማድረግ በ2009 በጀት ዓመት ብር 1,924,951.78 በመጨመር ክፍያ የተፈፀመ መሆኑን፣
2. ለሥራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን ጥናት ፕሮጀክት (JEG) የቢሮ አገልግሎት ግዥ የስድስት ወር ክፍያ ብር 291,387.60 በጨረታ መፈጸም ሲገባው በዋጋ ማወዳደሪያ ሁለት ተወዳዳሪዎችን ብቻ በማወዳደር ከግንቦት 30/2009 ዓ.ም ጀምሮበወር ብር 48,564.60 ለስድስት ወር የሚፀና ውል ተዋውሎ መከራየቱን፣
3. ባልተፈቀደ የሹመት መደብ ለኢንስቲትዩቶችና ለኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተርና ምክትል ዋና ዳይረሬክተርነት ማዕረግ ጥቅማ ጥቅም ለመወሰን ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት የተፃፈውን መሰረት በማድረግ ተሿሚ ላልሆኑ ለ4 የቢሮ ኃላፊዎች በወር በልዩነት በእያንዳንዱ ሰራተኛ ብር 2,711.00 በጠቅላላው ብር 86,752.00 ያላግባብ ተከፍሎ መገኘቱን እና ከተጠቀሱት ውስጥ የአንዱ ሠራተኛ ያላቸው የትምህርት ዝግጅት እና ቀድሞ ከነበሩበት መ/ቤት መልቀቂያ ከማህደራቸው ያልተገኘ መሆኑን፣
4. የመንግሥት ሠራተኞችአዋጅ 515/99 ክፍል 3 ከሚፈቅደውውጭ 8 ሠራተኞችንበማዛወርበአጠቃላይ በዓመቱ ውስጥ ብር 182,550.00 ያላግባብህጉከሚፈቅደውበላይተከፍሎመገኘቱን፣

5. ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ባልተፈቀደ መደብ፣ ባልተደለደለና ባልፀደቀ በጀት ያለአግባብ የደመወዝ ማስተካከያ በማድረግበጠቅላላው ብር 133,849.00 ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱን፣
6. ከክልል የመጡት የስራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን ጥናት ፕሮጀክት (JEG) አባላት ለግል ጉዳያቸው ወደ መጡበት ክልል ለበዓላት ሲሄዱ ከመንግስት በጀት ለትራንስፖርት በድምሩ ብር 74,424.00 ያለአግባብ የተከፈለ መሆኑን፣
7. ሚኒስቴርመ/ቤቱለተቀናጀ የሲቪል ሰርቪስ መረጃ አያያዝ ሥርአት(ICMIS) ከጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት ፀድቆ በመጣው የደመወዝ ስኬል መሠረት ማሠራት ሲገባው፣የመደበኛ ሠራተኛ የሆኑትን አንዴ በፕሮጀክቱ አንዴ ደግሞ በመደበኛው የደመወዝ ጭማሪ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በሁለቱም መዋቅር እያስተናገደ በመሆኑ በልዩነት ለ8 ሠራተኞች በድምሩብር 102,779.80 ያላግባብ በብልጫ ከፍሎ መገኘቱ፤ እንዲሁም የፕሮጀክቱ ማናጀር እና ምክትል ማናጀር ፀድቆ በመጣው የኮንትራት መዋቅር ሳይሆን፣በቋሚ ሰራተኞች እያሰራ መሆኑን፣
8. ማንኛውም የአገልግሎት እና የዕቃ ግዥዎች በግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሠረት መፈጸም ሲገባቸው ሚኒስቴር መ/ቤቱ፡-
    - በብር 11,960.00 ለብሄር ብሄረሰቦች ቀን በዓል የባጅ ግዥ ያለ ዋጋ ማወዳደሪያ በቀጥታ ግዥ ከጂቲ ማተሚያ ቤት የፈፀመ መሆኑን፣
    - በተለያየ ቀንና የደረሰኝ ቁጥር ያለምንም ውድድር ከተለያዩ አቅራቢ ድርጅቶች በድምሩ ብር 421,687.96 በቀጥታ ግዥ መፈፀሙን፣
    - ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበው ብር 80,500.00 ሆኖ ሳለ፣ ከፍተኛ ዋጋ ብር 169,640.00 ከአቀረበው ድርጅትበመገዛቱ ብር 89,140.00 ያለአግባብ በብልጫ ተከፍሎ መገኘቱ፣
    - በጨረታ ግዥ መፈጸም ሲገባው፣ ከተለያዩ አቅራቢዎች ተቆራርጦ በዋጋ ማቅረቢያ በአጠቃላይ ብር 10,013,266.63 ግዥ መፈፀሙን፣
9. በድምሩ ብር 32,200.00 ከደንብ ውጭ ከተማ ውስጥ ለተደረገ ዝውውር ውሎ አበል ተከፍሎ መገኘቱን፣
10. ለ29 ሠራተኞች በተለያዩ ክልሎች የለውጥና የመልካም አስተዳደር ሥራዎች ሱፐርቪዥን ለማድረግ በሚል በድምሩ በብልጫ ብር 170,982.00ውሎ አበል ተከፍሎአቸው መገኘቱን፣
11. ብር 3,233,339.71 በመ/ቤቱ በኩል ለሚሰጡ ስልጠናዎችና ስብሰባዎች ለተሳታፊዎች ሙሉ አገልግሎት ማለትም ቁርስ፣ ምሳ፣ እራት እና መኝታተሰጥቶ በተጨማሪ ሰልጣኞች እንደሥልጠናው ቆይታ ጊዜያቸው ግማሽ የቀን ውሎ አበል ተከፍሎ መገኘቱን፣

12.ሠራተኞች ለድጋፍ ወደ ተለያዩ ክልሎች ሲሄዱ በዕቅድ ጊዜ በሚዘጋጀው (TOR) እና የዓመት እቅድን በወር ብዛት መሰረት በማድረግ የክፍሉ ተጠሪ ስለቆይታው ማረጋገጫ ባላቀረበበትና በመስክ ሥራ መሆናቸው ሳይረጋገጥየአንድ ባለሞያ ብር 32,052.15 የውሎ አበል ክፍያን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉን፣

13.በድምሩ ብር 478,031.50 የተዘረጋ እና የተፈቀደ ሥርአት ሳይኖር ያለደንብና መመሪያ ለሽልማት፣ ለዋንጫና ለሰርተፍኬት ክፍያ መፈፀሙን፣

14.በብር 3,699,305.25 ባልተፈቀደ በጀት ለድጋፍ (ስፖንሰር) የተከፈለና ያለሂሳብ መደቡ ተመዝግቦ መገኘቱን፣

15.በድምሩ ብር 111,505.61 ያለአግባብ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ተከፍሎ መገኘቱን፣

16.የሠሌዳ ቁጥር 4-04266 ያለ ኢንሹራንስ ሽፋን የንብረት አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት በተፃፈ ደብዳቤ ያለአግባብ በተከሰተ አደጋ ከካዝና በብር 154,242.07 መኪናው እንዲጠገን መደረጉ፣

17. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሠሌዳ ቁጥር 4-14032 ጥገና እንዲደረግ ለኢትዮጵያ መድህን ድርጅት በጠየቀው መሠረት ድርጅቱ ባወጣው ጨረታ ዝቅተኛ ዋጋ ብር 926,473.72 ባቀረበው አሽናፊ ጋራዥ ጥገናው እንዲደረግ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ቢያሳውቅም፣ የሚኒስቴር መ/ቤቱ በሞኤንኮ ጋራዥ እዲጠገን በማስደረጉ ብር 1,498,573.36 እንዲከፈልና በልዩነት የሚታየውን ብር 572,099.64 የኢንሹራንስ ሽፋን እያለ ያለአግባብ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ካዝና በመብለጥ ተከፍሎ መገኘቱን፣

<u>የተሰብሳቢ ሂሳብ፣</u>

18.በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሂሳብ መግለጫ ሪፖርት በድምሩ ብር 23,590,414.87 ተሰብሳቢ ሂሳብ የሚታይ ሲሆን፣ በዝርዝር መነሻ ቋት ግን ብር 28,729,588.034 በመሆኑ ከመነሻ ሂሳብ ወይም ከመወራረጃ ሰነዱ ጋር ሲገናዘብ፣ ብር 5,139,173.16 ልዩነት ያለው መሆኑን፣

19.የመ/ቤቱ ሠራተኞች የነበሩት አቶ ካሳሁን ግርማ እና አቶ ገመቹ መለታ የወሰዱትን አበል በወቅቱ ያልተወራረደ ሂሳብ እንደተወራረደ ቢገልጽም፣በተገኘው የሂሳብ ቋት መሠረት ቀሪ ዕዳ ብር 24,864.39 አቶ ገመቹ መለታ እና ብር 25,830.38 አቶ ካሳሁን ግርማ ከ2006 በጀት ዓመት ጀምሮ በጠቅላላ ብር 50,697.77 ሳያወራርዱመገኘቱን፣

<u>የተከፋይ ሂሳብ፣</u>

20.ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለአቅራቢዎች ብር 5,662.86፣ ለመንግስት መስሪያ ቤቶች ብር 31,042.56፣ የተለያዩ ክፍያዎች ብር 355,987.62 እና የዋስትና ተከፋይ ብር 1,027,648.48 በጠቅላላው ብር

1,420,341.52 የተከፋይ ሂሳብ በሪፖርት የሚታይ ቢሆንም፣ ለማን ለማን እንደሚከፈልና ከመቼ ጀምሮ በተከፋይ ሂሳብ እንደሚታይ የሚገልጽ ሰነድ/ማስረጃ አለመቅረቡን፣

በጀት፣

21. የመደበኛው በጀት በተቀናጀ የፋይናንስ መረጃ አስተዳደር ሥርዓት /IFMS/ የተመዘገበው በብር 30,000.00 በማነስ የሚታይ መሆኑን፣
22. የ2009 የታወጀና የተተከለ በጀት ሳይኖር እና ዝውውር ሳይደረግ ከመደበኛ በጀት ብር 3,554,091.09 እና ከካፒታል በጀት ብር 1,344,497.50 በድምሩ ብር 4,898,588.59 ባልታወጀ በጀት እንደ ወጪ ተይዞ መገኘቱን፣
23. ብር 10,119,113.04 ከመደበኛው በጀት እና ብር 8,969,702.97 ከካፒታል በጀት በድምሩ ብር 19,088,816.01 ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ ሆኖ መገኘቱን፣

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 24በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሳ በእኛ አስተያየት የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሂሳብ መግለጫዎች ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም. የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም።

ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፣

ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊደረግባቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል።

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሲቪል ሰርቪስ መረጃ አያያዝ ስርዓት(ICMIS) መረጃዎችን ከክልሎች ጋር በመጣመር ለጀመረው ዝርጋታ ድጋፍ በማድረግ ሥርአቱ እንዲጠቀሙ ባልተደረገበት እና እየሰራ መሆኑን ሳያረጋግጥ በድምሩ ብር 1,032,637.58 በ2009 በጀት ዓመት ተከፍሎ መገኘቱን፣
- ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የተመደበለት በጀትና ሥራ ላይ ያዋለው ሂሳብ ሲመዛዘን፣ ከመደበኛ በጀት ብር 28,446,992.95 እና ከካፒታል በጀት ብር 44,426,074.32፣ በድምሩ ብር 72,873,067.27 ያልተሰራበት በጀት መገኘቱን፣

ሌሎችጉዳዮች፣

- በንብረት ወጪ ደረሰኝ ሞዴል 22 ከንብረት ክፍል በግራውንድ (B2) 27 ጎማ፣19 ካለማደሪያ እና 15 ፍላፐ የተገኙና ንብረቶቹ ወጪ ሆነው የተቀመጠ መሆኑን፣

- ለፑል አገልግሎት የሚውሉ መኪኖች የተጠቀሙበትን የነዳጅ መጠንና ከሸፈኑት የኪ/ሜትር በየጊዜ ምዝገባ እየተከናወነ ቢሆንም የማስታረቅ ስራ በጌጅ በማንበብ በርቀቱ እንደማይሰራ እና በግምት የሚሰላ መሆኑን፣
- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለገዛቸው ዕቃዎች ሞዴል19 በማንዋል እና በሲስተም እየተቆረጡ በመሆኑ የተቀናጀ የሂሳብ አያያዝ ስርአት ሙሉ ለሙሉ እየተሠራበት አለመሆኑ፣
- በ2008 የኦዲት አስተያየት መሠረት በተወሰኑ ግኝቶች ላይ የእርምት እርምጃ አለመወሰዱን፣

የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር

የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች

መግቢያ፣

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የመ/ቤቱን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

ዓላማ፣

የዚህ ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የመ/ቤቱ የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ምላሽ እንዲሰጡበት ለማስቻል ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት፣

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፣

- የሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ ሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን፣ ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ኦዲት ማድረግን ይጨምራል፡፡

ቀጥለው በተመለከቱት የኦዲት ግኝቶች ላይ የማሻሻያ ሀሳቦችን ለመስጠት በሂሣብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡

ይሁን እንጂ ኦዲቱ በፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የመ/ቤቱ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር የ2009 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1. <u>የወጪ ሂሳብ፣</u>

1.1.1 <u>ግኝት</u>፣ <u>በውል ሳይካተት ያለአግባብ የተከፈለ የ15% ጭማሪ የቢሮ ክራይ፣</u>

የፌዴራል መንግስት የፋይናንስ ኃላፊነት መመሪያ ቁጥር 6/2003 ክፍል ሁለት የመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች በቁጥር 6(ለ) "የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ላይ በመመርኮዝ የወጡት መመሪያዎች በመ/ቤቱ ውስጥ በተሟላና ተገቢ በሆነ መንገድ ሥራ ላይ መዋላቸውን በማረጋገጥ ረገድ ላይ ተጠያቂነት እንዳለባቸው" ሲል ይገልፃል፡፡

በተጨማሪም የፌዴራል መ/ቤት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ/2002 ዓ.ም. አንቀጽ 16.27 ስለውል መፈራረም፣ አንቀጽ 16.27.3 «በአቅራቢው እና በመንግሥት መ/ቤቱ መካከል የሚደረገው ውል የሁለቱን ወገኖች ኃላፊነት በግልጽ ማመልከት ያለበት« እንደሆነ ተገልጿል፡፡ በመቀጠልም ውሉ ከሚያካትታቸው ጉዳዮች በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል (ሀ) "በውሉ የሚቀርበው ዕቃ፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራ ወይም የምክር እና ሌሎች አገልግሎቶች ዓይነት፣ ጥራት፣ ብዛት፣ የሚቀርብበት አኳኋን ወይም የማስረከቢያውን ጊዜውን፣ የሚከፈለውን አጠቃላይ እና ነጠላ ዋጋ መጠን፣ የአከፋፈል ሁኔታ እና የክፍያ ጊዜውን፣" በማለት ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሕንፃ ኪራይ ትግስትደነቀሪልስቴትየካቲት 7 ቀን 2003 ዓ.ምጀምሮስፋቱ 4687.55 በዓመትበብር 8,437,927.50 እስከ 2005 ዓ.ምየቢሮአገልግሎትግዥየፈፀመሲሆን፣ በውሉ ላይ በግልፅ ባልተካተተከ2006 ዓ.ምጀምሮ ያለአግባብበየዓመቱ የ15% የዋጋ ጭማሪ በማድረግ በ2009 በጀት ዓመት በወጪ ማስመስከሪያ 09431 በ27/11/2008 በጀት ዓመት ብር 1,924,951.78 በመጨመር ክፍያ የፈፀመ መሆኑን እና ከ2006 እስከ 2009 ዓ.ም ድረስ በድምሩ ብር 6,320,036.58 ጭማሪ ማድረጉ ተረጋግጧል፡፡ የሂሳብ ዝርዝሩም እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡-

ዓመተ ምህረት	ቀድሞ የነበረው ዋጋ	የተጨመረ ዋጋ 15%	ጠቅላላ የተከፈለ ዋጋ
2006	8,437,927.20	1,265,689.13	9,703,616.63
2007	9,703,616.63	1,492,056.22	11,195,672.42
2008	11,195,672.42	1,637,339.45	12,833,011.87

2009	12,833,011.87	1,924,951.78	14,757,963.66
	ልዩነት	6,320,036.58	

1.1.2 በኦዲቱ ወቅት የተሰጠ ምላሽ፣

የህንፃና ቢሮ ኪራይ፣

በቅድሚያ መ/ቤቱ ተከራይቶ የነበረበት ህንፃ ለአገሪቱ ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት የሚፈለግ መሆኑ ተገልጾ በአስቸኳይ እንድንወጣ የታዘዘው በጠቅላይ ሚ/ሩ ጽ/ቤት ነው፡፡ ከትዕግስት ደነቀ ሪል ስቴት ጋር የተደረገው ሕንፃ ኪራይ ውል በየዓመቱ በሚታደስበት ወቅት 15% ጭማሪ አከራዩ በዝርዝር በሚያቀርባቸው ምክንያቶች በተለይም የቢሮ ኪራይ ዋጋ ከአካባቢው ኪራይ ዋጋ ዝቅተኛ መሆኑን፤ እንዲሁም የአስተዳደራዊና የጥገና ወጪዎች በመጨመራቸው ወዘተ ምክንያት እያቀረበ እንድንጨምር ይጠይቃል፡፡ ሆኖም መ/ቤቱ የዋጋ ጭማሪ ከማድረጉ በፊት የተጠየቀዉ ዋጋ ከአካባቢዉ ተመሳሳይ ይዘትና ደረጃ ካላቸዉ ህንጻዎች ዋጋ ጋር ለማነጻፀር ጥናት ተደርጎ የተጠየቀዉ ጭማሪ ያልተጋነነና ዝቅተኛ መሆኑ ሲረጋገጥ ጭማሪዉ ይደረግ ነበር፡፡ ከዚህ አመታዊ ጭማሪ ለመላቀቅና በአነስተኛ ዋጋም ለመከራየት ከሶስት ጊዜ በላይ በየዓመቱ ኮሚቴ ተዋቅሮ ያፈላለግን ቢሆንም አሁን ካለንበት ህንፃ በዋጋም ለስራም የተሻለ ማግኘት አልተቻለም፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎንም በ2003 ዓ..ም ለአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር የራሳችን ሕንጻ ለመገንባት የመሬት ጥያቄ አቅርበን ምላሽ አልተሰጠም፡፡ በመቀጠልም ለመንግስት ተመሳሳይ ጥያቄ አቅርበን በከፍተኛ አመራር ደረጃ አሁንም ክትትል እየተደረገ ይገኛል፡፡

በመሆኑም መ/ቤቱ እነዚህን ጥረቶችን አድርጎ ከአከራዩም ጋር ክርክርና ውይይት በማድረግ አከራዩ ጭማሪ ካልተደረገላቸው ሕንፃውን ለቀን እንድንወጣ ጥያቄ በየጊዜዉ በጽሁፍና በአካልም ጭምር እየመጡ የሚጠይቁን በመሆኑ አማራጭ በማጣትና መ/ቤቱን መዝጋት ስለማይቻል ጭማሪው ሲደረግ ቆይቷል፡፡ ይህን ችግር ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር አሳዉቀናል፤ የሚታወቅም ነው፡፡ አስፈላጊ ከሆነ ዝርዝር ጉዳዮች ከወጪ ሰነዶች ማየት ይቻላል፡፡

1.1.3 ስጋት፣

- ለቢሮ አገልግሎት ተብሎ ለአንድ ዓመት ብቻ ውል መግባቱ አከራዩ በየጊዜው እንደፈለገ ውሉን እንዲያሻሽል ሊያደርገው ይችላል፣ ይህም የመንግስት ገንዘብ ያላግባብ ክፍያ እንዲፈፀም ሊያደርገው ይችላል፡፡

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሁለት ቦታ ላይ የቢሮ አገልግሎት ግዥ መፈፀሙ የመንግስት ገንዘብ ያላግባብ እንዲባክን ያደርገዋል፡፡

1.1.4 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ማንኛውንም የዕቃና የአገልግሎት ግዥ ሲፈጽም በውል ከተካተተው ውጭ ክፍያ መፈጸም የለበትም፡፡ የውል ይዘትም እንዲለወጥ (እንዲሻሻል) ከተደረገ የሚሻሻለው ውል የመ/ቤቱን ጥቅም እንዲያስጠብቅ በማድረግ መዋዋል ይኖርበታል፡፡ የቢሮ አገልግሎት ግዥ ሲፈጽም እና የዋጋ ጭማሪ ሲያደርግ አግባብ ባለው መልኩ የግዥ ስርዓቱን የተከተለ መሆን አለበት፡፡ እንዲሁም የቢሮ አገልግሎት ግዥ ሲፈጽም በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መሆን አለበት፡፡ ለወደፊቱም መሰል ስህተት እንዳይፈጸም ቁጥጥር እና ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

1.2.1 <u>ግኝት፣በግልፅ ጨረታ መገዛት የነበረበት የቢሮ አገልግሎት</u>

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ አንቀጽ 23 ውስን ጨረታ ግዥ አፈፃፀም ንዑስ አንቀጽ 23.2.1 ፊደል ሀ ላይ በተገለጸው መሰረት ዕቃው፣ የግንባታ ዘርፍ ስራው ወይም አገልግሎቱ ከተወሰኑ አቅራቢዎች ብቻ የሚገኝ ሲሆን፣ የጨረታ ጥሪው ደብዳቤ ለሁሉም አቅራቢዎች በአድራሻቸው ተዘጋጅቶ መላክ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በመቀጠልም ፊደል (ለ) ግዥን በውስን ጨረታ ለመፈጸም ቢያንስ አምስት እጩ ተወዳዳሪ መመረጥ እንዳለበት መመሪያው በግልፅ አስቀምጧል፡፡ በዚህ መሰረት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በመመሪያው መሰረት የአገልግሎት ግዥዎችን ስለመፈፀሙ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ የሥራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን ጥናት ፕሮጀክት (JEG) ቀድሞ ከሚሰራበት የኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት በመውጣት የስድስት ወር ክፍያ ብር 291,387.60 በጨረታ መግዛት ሲገባው ሁለት ተጫራቾችን ብቻ በማጫረት ከአቶ ተስፋዬ ወርቁ ተፈሪ እና ከወ/ሮ አልማዝ በየነ ከግንቦት 30/2009 ዓ.ም ጀምሮ ስፋቱ 231.26 የሆነ ሕንፃ በወር ብር 48,564.60 ለስድስት ወር የሚፀና ውል ተዋውሎ መከራየቱን እና በ09/10/2009 ዓ.ም በደረሰኝ ቁጥር 012299 የአንድ ወር ብር 48,564.60 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

1.2.2 <u>በኦዲቱ ወቅት የተሰጠ ምላሽ፣</u>

<u>የጀኢጂ ፕሮጀክት ቢሮ ኪራይ በተመለከተ</u>

ለJEG ፕሮጀክት ቢሮ የተከራየነው ቀደም ሲል የነበሩበት መ/ቤት የቢሮ እጥረት በማጋጠሙና በመ/ቤታችን ውስጥ ምንም ትርፍ ቢሮ ባለመኖሩ ተቸግረን ነው፡፡ ለስድስት ወራት ውል የገባነው ፕሮጀክቱ በስድስት ወራት ውስጥ እንዲጠናቀቅ በመወሰኑ ነው፡፡

1.2.3 ስጋት፣

•በግልፅ ጨረታ ሂደት መገዛት የነበረበት የቢሮ አገልግሎት በሁለት ተወዳዳሪዎች ብቻ ግዥው መፈፀሙ እና ለ6ወር ብቻ ተብሎ ውል መግባቱ አከራዩ በየጊዜው እንደፈለገ ውሉን እንዲያሻሽል ሊያደርገው ይችላል፣ ይህም የመንግስት ገንዘብ ያላግባብ ክፍያ እንዲፈፀም ሊያደርገው ይችላል፡፡

1.2.4 የማሻሻያ ሀሳብ፣

የቢሮ አገልግሎት ግዥ ሲፈጽም ከተቀመጠው የገንዘብ መጠን በላይ ከሆነ በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ የግዥ ስርዓቱን የተከተለ መሆን አለበት፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለ6 ወር ብቻ ውል መዋዋል የመ/ቤቱን ጥቅም እንዲያስጠብቅ ስለማያደርገው ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሲዋዋል የመ/ቤቱን ጥቅም የሚያስከብር በማድረግ መዋዋል ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም መሰል ስህተት እንዳይፈጸም ቁጥጥር እና ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

1.3.1 ግኝት፣ በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ የተሰጠ ሹመት፣

የኢትዮጵያ ፌደራል ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላት ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣ አዋጅ 916/2008 ክፍል 2 ስር የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር በሚለው ስር ሹመትን በተመለከተ የሚገልፅ ነገር የለም፡፡ የኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 70 ንዑስ አንቀጽ 9 “ከፍተኛ የመንግስት የሲቪል ሹመቶችን ይሰጣል፡፡” የሚል ሲሆን የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር በአዋጅ አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ በ “የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶችን የውስጥ አደረጃጀት አግባብነት መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፤ በአደረጃጀት ማሻሻያ ጥናት ላይ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፡፡” ይሁን እንጂ፡-

- የሚኒስቴሩ መ/ቤት አደረጃጀት በተመለከተ በ02/02/2008 ዓ.ም በቁጥር ሲሰሚ/ሚጽ-ረ/09/08 ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት በ7 መደቦች የቢሮ ኃላፊ ሹመት እንዲፈቀድለት በደብዳቤው ገልጿል፡፡ ነገር ግን መፈቀዱን የሚገልፅ ማስረጃ ሳይቀርብ፣ ሹመት መስጠት የሚኒስቴር መ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር ሳይሆን የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት እያለ ባልተፈቀደ የሹመት መደብ ለ4 የቢሮ ኃላፊዎች ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት የተፃፈውን ለኢንስቲትዩቶችና በዋና ዳይሬክተርና በምክትል ዋና ዳይሬክተርነት ማዕረግ ለዳይሬክተሮች የተፈቀደውን ጥቅማ ጥቅም ስለመወሰን በሚያዚያ 16 ቀን 2004 ዓ.ም በቁጥር መ80/899/62 የተፃፈውን መሰረት በማድረግ ተፈፃሚ እንዲሆን ሚኒስቴር መ/ቤቱ አዟል፡፡ ይህም በመሆኑ በወር በልዩነት በእያንዳንዱ ሰራተኛ ብር 2,711.00 የሚታይ ሲሆን እስከ አሁን የተከፈለ በብልጫ በጠቅላላው ብር 86,752.00 ያላግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

.ቁ	የሰራተኛስም	የደሞዝመጠን	**የደብዳቤ**		መከፈልየነበረበት	ያለውልዩነት	ምርመራ
			ቀን	ቁጥር			
1	**አቶ ብረሃኑ ንጉሴ**	8,852.00	23/12/08	ፐሰሚ/ሚጸ1/111/08			**ያላቸው የትምህርት ዝግጅት ያልቀረበ ቀድሞ ከነበሩበት መልቀቂያ የሌለ**
		13,012.00	20/06/09	ፐ/ሰ/ሰ/ሀ/ል/ሚ/ሰሀ/በ 44/3	10,567.00		
		13,278.00	01/07/09	ፐ/ሰ/ሰ/ሀ/ል/ሚ/ሰሀ/ በ44/4	10,567.00	2,711.00*8=21,688.00	
2	**አቶ ተስፋይ በላቸው**	7,936.00	12/04/08	ፐ/ሰ/ሰ/ሀ/ል/ሚ/ሰሀ/ ተ61/9			
		8,852.00	15/06/08	ፐ/ሰ/ሰ/ሀ/ል/ሚ/ሰሀ/ ተ61/10			
		13,012.00	20/06/09	ፐ/ሰ/ሰ/ሀ/ል/ሚ/ሰሀ/ ተ61/12	10,567.00	2,445.00	
		13,278.00	01/07/09	ፐ/ሰ/ሰ/ሀ/ል/ሚ/ሰሀ/ ተ61/13	10,567.00	2,711.00*8=21,688.00	
3	**አቶ መብራቱ ካሳ ተሰማ**	7,936.00	12/04/08	ፐ/ሰ/ሰ/ሀ/ል/ሚ/ሰሀ/ መ50/25			
		8,852.00	15/06/08	ፐ/ሰ/ሰ/ሀ/ል/ሚ/ሰሀ/ መ50/27			
		13,012.00	20/06/09	ፐ/ሰ/ሰ/ሀ/ል/ሚ/ሰሀ/ መ50/28	10,567.00	2,445.00	
		13,278.00	04/07/09	ፐ/ሰ/ሰ/ሀ/ል/ሚ/ሰሀ/ መ50/29	10,567.00	2,711.00*8=21,688.00	
4	**አቶ ተስፋይ አጥሬ**	7,936.00	12/04/08	ፐ/ሰ/ሰ/ሀ/ል/ሚ/ሰሀ/ ተ35/7			
		8,852.00	15/06/08	ፐ/ሰ/ሰ/ሀ/ል/ሚ/ሰሀ/ ተ35/8			
		13,012.00	20/06/09	ፐ/ሰ/ሰ/ሀ/ል/ሚ/ሰሀ/ ተ35/9	10,567.00	2,445.00	
		13,278.00	01/07/09	ፐ/ሰ/ሰ/ሀ/ል/ሚ/ሰሀ/ ተ35/10	10,567.00	2,711.00*8=21,688.00	
በጠቅላላደምርብር						86,752.00	

- እንዲሁም የፌደራል መንግስት ሠራተኛ አዋጅ 515/99 ክፍል 7 አንቀጽ 59 ንዑስ አንቀጽ 1- “ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት እና ኤጀንሲው ስለእያንዳንዱ ቋሚም ሆነ ጊዜያዊ ሠራተኛ አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች የሚይዝ የግል ማህደር እንዲኖር ያደርጋሉ፡፡” ይላል፡፡ ይሁን እንጂ ሚኒስቴሩ መ/ቤቱ አቶ ብረሃኑ ንጉሴ የመ/ቤቱ ሠራተኛ ያላቸው የትምህርት ዝግጅት እና ቀድሞ ከነበሩበት መ/ቤት መልቀቂያ ከማህደራቸው የሌለ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

1.3.2 <u>በኦዲቱ ወቅት የተሰጠ ምላሽ፣</u>

የቢሮ ኃላፊዎች ሥራ መደብ፣ ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም በሚመለከት ጥቅምት 2 ቀን 2008 ዓም በቁጥር ሲሰሚ/ሚጽ- ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት በተጻፈ ደብደቤ መነሻነት የመ/ቤት ተዕልኮ እንዲሳካ በቂ ዕውቀትና ልምድ ያላቸው ኃላፊዎችና ባለሙያዎችን መ/ቤቱ መያዝና ማቆየት እንዲችል ሌሎች ባለሙያዎች በማካተት መጠነኛ የደመወዝ ማስተካከያ እንዲደረግ ጥያቄ ቀርቦ በአመራር ደረጃ ውይይት በሚደረግበት ወቅት በመነሳቱና ይህም ተቀበይነት በማግኘቱ የ7 ቢሮ ኃላፊዎችና ሌሎች ሠራተኞች ያካተተ ህዳር 15 ቀን 2008 ዓም ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ጥያቄ ቀርቦ ህደር 17 ቀን 2008 ዓም በደብዳቤ ቁጥር ጠ80-813/2 ተፈቅዷል፡፡

የቢሮ ኃላፊዎች መደብ ጥናት በዝርዝር ተለይቶ ለመንግስት ቀርቦ የተፈቀደው ተቋማትን የሚመሩ ሳይሆኑ የቢሮ ኃላፊ ሆነው የዋና ዳይሬክተር ደመወዝና ጥቅማ ጥቅሞችን አግኝተው የመ/ቤቱ የበላይ አመራርን ከሌሎች ዳይሬክቶሬቶች አንድ ደረጃ ከፍ ያለ የሥራ መደብ ይዘዉ /ዝርዝርና ዓላማውን ማየት ይቻላል/ና በመ/ቤቱ ውስጥ ለመ/ቤቱ የበላይ አመራር ተጠሪ እንዲሆኑና እንዲደግፉ ታስቦ የተፈጠረ መደብ ነው፡፡ በመሆኑም ለጠቅላይ ሚ/ሩ አቅርበው በመ/ቤት ውስጥ ለመ/ቤቱ የበላይ አመራር ተጠሪ የሆነን ኃላፊ የማሾም አሰራር ባለመኖሩና አስፈላጊም በለመሆኑ ጭምር ነው፡፡ ይህ አሰራር በሌሎች መንግስት መ/ቤቶች ውስጥም እንደተቋሙ የሥራ ስፋት የበላይ አመራርን የሚያግዙ ኃላፊዎች ተመድበው የሚሰሩበት አሰራር ነው፡፡ ጥያቄው የቀረበውና ፍቃድ የተገኘው በዚህ መልክ ስለሆነ በመንግስት መ/ቤቶች ውስጥ ለዋና ዳይሬክተሮች የተፈቀዱትን ጥቅማ ጥቅሞች እንዲያገኙ ተደርጎ ክፍያው እየተፈፀመ ይገኛል፡፡

ከሌላ መ/ቤት የተመደበው ቢሮ ኃላፊን በተመለከተም ከኣሁን በፊትም በክልልና በፌዴራል ተቋማት ተሹመዉ በኃላፊነት ሲሰሩ የነበሩ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት አባልና ለቦታው ከፍተኛ የሥራ ልምድ፣የትምህርት ደረጃ፣ የማፈጸም ብቃትና ስነ ምግባር እንዳላቸው ታይተው በድርጅት አሰራር የተመደቡ ናቸው፡፡ በቀጣይ ያላቸው መረጃ የእሳቸውም ሆነ የሌሎች አመራሮች እንዲደራጅ መደረጉ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

1.3.3 <u>ስጋት፣</u>

በአዋጁ ከተሰጠ ስልጣን ከሚፈቅደው ውጭ መስራት መንግስት ያወጣውን ህግና ደንብ ተፈፃሚ እንዳይሆንና ህጎች እንዲጣሱ መንገድ ሊከፍት ይችላል፡፡

1.3.4 የማሻሻያሀሳብ፣

- ለሚኒስቴርመ/ቤቱበ02/02/2008 ዓ.ምበቁጥርሲሰሚ/ሚጽ-ሪ/09/08 ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት የጠየቀበትን በኦዲት ወቅት የተጠቀሰውን ደብዳቤ ምላሽ የተሰጠው በመሆኑና የደብዳቤውም መንፈስ የሚያስረዳው የመ/ቤቱን መዋቅርና መደብ የተፈቀደ መሆኑን የሚገልጽ በመሆኑ የተጠየቀውን ግኝት በማስመልከት ማስረጃ ካለ እንዲቀርብ፡፡ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድና ከሚመለከታቸውሰራተኞችበብልጫየተከፈለውከእያንዳንዳቸውብር 21,688.00 በጠቅላላው ብር 86,752.00 እንዲሰበሰብና የሚኒስትሮች ምክር ቤት ጥር 26 2009 ዓ.ም ባካሔደው አምስተኛ የምርጫ ዘመን 22ኛ መደበኛ ስብሰባ መንግስት ከጥር 1 ቀን 2009 ዓ.ም ባስተላለፈው የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር የደሞዝ ስኬል መሸጋገሪያ ሠንጠረዥ መሰረት ተግባራዊ እንዲሆን እና አሁንም በተፈቀደው መሰረት እንዲስተካከል እንዲደረግና አፈፃፀሙ ሪፖርት እንዲደረግልን በተጨማሪም የፈቀደው አካል ተጠያቂ ሊደረግ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም መሰል ስህተት እንዳይፈጸም ቁጥጥር እና ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴርመ/ቤቱሰራተኞችንሲደለድልምሆነሲያዘዋውርህግንየተከተለ እና የተሟላ መረጃ መያዝ አለበት፡፡ አሁንም የትምህርት ማስረጃው ቀድሞ ይሰራበት ከነበረው መስሪያ ቤት በማምጣት ፋይሉን በማያያዝ አፈፃፀሙ ሪፖርት በማድረግ ይህ በኦዲት ወቅት የታየው በናሙና ስለሆነ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሰው ሀይል አደረጃጀት ማጣራት አለበት፡፡

1.4.1 ግኝት፣ ያላግባብ ህጉ ከሚፈቅደው ውጭ ተዛውረው ለሠራተኞች የተከፈለ፣

የፌደራልመንግስትሠራተኛአዋጅ 515/99 ክፍል 3 አንቀጽ 28 ከሌላመስሪያቤትየሚደረግዝውውርንዑስአንቀጽ 1 እና 2 "እንድየመንግስትመሥሪያቤትለሥራውአስፈላጊሆኖሲያገኘውናላኪናተቀባይመሥሪያቤቶችእን ዲሁምሠራተኛውሲስማሙአንድንየመንግስትሠራተኛእኩልበሆነደረጃናደመወዝተመሣሣይወደ ሆነየሥራመደብኤጀንሲውንበማሳወቅአዛውሮማሠራትይችላል፡፡" የሚለውንለማረጋገጥኦዲትሲደረግ፣ሚኒስቴርመስሪያቤቱበ28/06/2008 ዓ.ም.የስብሰባቦታ 5ኛፎቅአዳራሽ"የሠራተኛዝውውርአስመልክቶአሁንበተደረገውአዲስአደረጃጀትደረጃውእንዳለሆ ኖየደመወዝለውጥያለውበመሆኑበዝውውርየሰውኃይልለማሟላትእንዲቻልለመወሰን"በማለትከአ መለከቱት"32 ሠራተኞችውስጥ 11 አመልካቾችእንዲዛወሩእስከ 5 እርከንድረስእንዲቀጠሩየፈቀድንመሆኑን"በማለትበናሙና ከታዩት ውስጥ 8 ሠራተኞችበዝውውርከአዋጁውጭበማዛወርከህምሌ 1/2008 እስከ ታህሳስ 30/2009በየወሩ

በድምሩ ብር 12,800.00 በብልጫየተከፈለና በአጠቃላይ የስድስት ወራት ብር 76,800.00 (12,800.00*6)፣ እንዲሁም ጥር 01 2009 ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 2009 በየወሩ በድምሩ ብር 17,625.00 በብልጫየተከፈለናበአጠቃላይ የስድስት ወራት ብር 105,750.00 (17,625.00*6) በአጠቃላይ በዓመቱ ውስጥ ብር 182,550.00 ያላግባብህጉና መመሪያውከሚፈቅደውውጭተከፍሎተገኝቷል፡፡**ዝርዝሩቀጥሎቀርቧል፡፡**

የሠራተኛ ስም	ያገኝየነበረው		የተዛወረበት		ከሀምሌ 1/2008 ጀምሮ ልዩነት	ከጥር ጀምሮ የሚከፈል ደሞወዝ	መከፈል የነበረበት	ከጥር 1/2009 ጀምሮ ልዩነት
	ደረጃ	ደሞዝ	ደረጃ	ደሞዝ				
ሻምበልበሪሁን እንየው	ፐሣ-9	5,781.00	ፐሣ-9	7,936.00	2,155.00	9,849.00	7,647.00	2,202.00
አቶአዱኛበቀለ	ፐሣ-9	5,781.00	ፐሣ-9	7,936.00	2,155.00	9,849.00	7,647.00	2,202.00
ወ/ሮብዙነሽቡ ሽራ	ፐሣ-7	4,461.00	ፐሣ-7	6,291.00	1,830.00	7,936.00	6,036.00	1,900.00
ወ/ሮሠርካለም ዱጋሣ	ፐሣ-6	3,909.00	ፐሣ-6	5,538.00	1,629.00	7,364.00	5,304.00	2,060.00
ወ/ሮማርታጳው ሎስ	ፐሣ-8	5,081.00	ፐሣ-8	7,081.00	2,000.00	8,852.00	6,809.00	2,043.00
አቶግርማዘሪሁ ን	ሹፌር -1	1,843.00	ሹፌር-1	1,916.00	73.00	2,748.00	2,628.00	120.00
ወ/ሮዘውትርተ መስገን	ደረጃ-2	3,909.00	ደረጃ-2	4,867.00	958.00	10,359.00	5,304.00	5,055.00
አቶብረሃኑታደ ሰ	ፐሣ-8	5,081.00	ፐሣ-8	7,081.00	2,000.00	8,852.00	6,809.00	2,043.00
ከሀምሌ 1/2008 ጀምሮ ድምር					12,800.00	ከጥር1/2009 ጀምሮ ድምር		17,625.00
❖ ጠቅላላ ድምር የዓመቱ ብር 182,550.00								

1.4.2 <u>በኦዲቱ ወቅት የተሰጠ ምላሽ</u>፣

መ/ቤቱበወቅቱበባለሙያእጥረትምክንያትተግባርናኃላፊነቱንመወጣትበማይችልበትደረጃላይበ መድረሱየተነሳጥናትተደርጎበቀረበውየመፍትሔሃሳብመሰረትለመ/ቤቱመጠነኛማስተካከያእንዲ ደረግለጠቅላይሚ/ርጽ/ቤትጥያቄቀርቦበመፈቀዱለመ/ቤቱመጠነኛየደመወዝማስተካከያበመደረጉ ቀደምሲልየነበሩየስራመደቦችደረጃደመወዝተሻሽሏል፡፡

በመሆኑምየመ/ቤታችንሥራመደቦችደመወዝከሌሎችመ/ቤቶችየፐብሊክሰርቪስየሥራመደቦችደ መወዝበመለየቱወደተቋማችንበተመሳሳይየሥራመደብያዘዋወርናቸውባለሙያዎችደመወዝበዚህ ምክንያትየደመወዝልዩነትየተፈጠረእንጂ

እርከንለእነርሱብቻገባተደርጎየተከፈለአልነበረም፡፡ዝውውሩምበተመሳሳይየሥራደረጃዎችመካከ

ልየተፈፀመሲሆንለምሳሌፕሣ-9ንበፕሣ-9

የማዘዋወርስራየተከናወነነው፡፡ዝውውሩምበደንቡመሰረትበሰራተኛውጥያቄናሁለቱመ/ቤቶችባደረ ጉትስምምነትመነሻህጉንተከትሎየተፈጸመነው፡፡

1.4.3 ስጋት፣

በአዋጁ ከተሰጠ ስልጣን ከሚፈቅደው ውጭ መስራት መንግስት ያወጣውን ህግና ደንብ ተፈፃሚ እንዳይሆንና ህጎች እንዲጣሱ መንገድ ሊከፍት ይችላል፡፡

1.4.4 የማሻሻያሀሳብ፣

ሚኒስቴርመስሪያቤቱለወጣውአዋጅ፣ደንብናመመሪያተግባራዊማድረግአለበት፡፡ደንቡ በሚለው መሠረት የስራ ደረጃ ብቻ ሳይሆን የደመወዝ መጠኑም ተመሳሳይ መሆን እንዳለበት የተገለጸ ስለሆነ በኦዲት ከታየው በተጨማሪ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሰው ሀይል አደረጃጀት ማጣራት አለበት፡፡ በመሆኑም የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድና 5 እርከን ገባ ተብሎ ዝውውሩ እንዲፈፀም ከፈቀደው አካል ያላግባብ የተከፈለው የመንግስት ብር 182,550.00 እንዲሰበሰብ እንላለን፡፡

1.5.1 ግኝት፣ያለአግባብ በቃለ ጉባኤ የደመወዝ ማስተካከያ ተደርጎ ክፍያ የተፈጸመ፣

ጊዜያዊወይምኮንትራትቅጥርበተመለከተከሲቪልሰርቪስሚኒስቴርበቁጥር 30/ጠ18/22/459 በ16/04/2005 ዓ.ም "ባልተለመደእናለዘላቂነትበሌለውየስራመደብበኮንትራትወይምበጊዜያዊነትተቀጥረውየነበሩሠራ ተኞችቅጥርእንዲቋረጥሆኖበአስቸኳይእንዲሰናበቱእናከየካቲት 30 2005 ዓ.ምበኃላበኮንትራትወይምበጊዜያዊነትቅጥርእንዳይፈፀምበማለትለፌደራልመስሪያቤቶችመመ ሪያውየተላለፈ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ቀድሞ ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት በተፈቀደው የስራምዘናናደረጃአወሳሰንጥናትፕሮጀክት (JEG) ለሚያጠናው ከየመስሪያቤቶችናክልሎችበተውጣጡባለሞያዎችእየተሰራ መሆኑን እየታወቀ ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ባልተፈቀደ መደብ፣ በሂሳብ መደብ 2111101 (6111- ለሰራተኞች የሚከፈል ደመወዝ ክፍያ) ባልተያዘና ባልፀደቀ በጀት በማዘዋወር ያለአግባብ ሚኒስቴርመስሪያቤቱ ለዚሁ ጥናት ተብሎ ቀድሞ ከኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት ተመድበው እየሰሩ እያለበኮንትራትሠራተኛ ሁለት(2) ሠራተኞችየቀጠረሲሆን፡-

1. ወ/ሮገላዬብርሃኑከ2004 ዓ.ምጀምሮ ለስራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን ጥናት ፕሮጀክት (JEG) ከኢትዮጵያሥራአመራርኢንስቲትዩትተመድበውእየሰሩእያለሚኒስቴርመ/ቤቱ ህዳር 06

ቀን 2009 ዓ.ምበፃፈውደብዳቤለስድስትወርበየወሩብር 7,936.00 እናቶፕ አፕበወር 2,500.00 እየተከፈለከህዳር 1 ቀን 2009 ዓ.ምጅምሮየተቀጠሩሲሆን፣

- ከህዳር እስከ ታህሣሥ የሁለት ወር በድምሩ ብር 15,872.00 (7936.00*2) ያለአግባብ የተከፈለ መሆኑን፣
- የካቲት 20/2009 ዓ.ምየሚኒስቴሮችምክርቤትከጥር 1 2009 ዓ.ምጀምሮለመንግስትመስሪያቤቶችየደመወዝስኬልማስተካከያእንዲደረግበተወሰነውመሰረትከብር 7,936.00 ወደብር 9,849.00 በማሳደግ ከጥር እስከ ሚያዝያ በድምሩ ብር 39,396.00 (9849.00*4) ያለአግባብ የተከፈለ መሆኑን፣
- ሠራተኛዋ የደመወዝ ጭማሪ ካልተደረገ እንደሚለቁ በመግለፃቸው በግንቦት 28 ቀን 2009 ዓ.ም በተካሄደው ቃለ ጉባኤ 5 እርከን ገባ ተብሎ እንዲቀጠር በሚል ሚያዚያ 18 ቀን 1989 ዓ.ም በቁጥር መ38/ተ56/3/51 እና መጋቢት 4 ቀን 1989 ዓ.ም በቁጥር መ30/ጠ18/329 በመጥቀስ ሰኔ 07 ቀን 2009 ዓ.ም በቁጥር ፕ/ሰ/ሀ/ል/ሚ/ሰሀ/734/2 በተፃፈ ደብዳቤ መሰረት ከብር 9,849.00 ወደ ብር 11,720.00 በማሳደግ ከግንቦት እስከ ሰኔ በድምሩ ብር 23,440.00 (11,720.00*2) ያለአግባብ የተከፈለ መሆኑን፣

በድምሩ ብር 78,708.00 ባልተፈቀደ መደብ፣ ባልተያዘና ባልፀደቀ በጀት ያለአግባብ ተከፍሏል፡፡

2. ወ/ሮ ስርጉት ሚሸል ቀድሞ ይሰሩበት ከነበረው ለስራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን ጥናት ፕሮጀክት (JEG) ከኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት ተመድበው እየሰሩ እያለ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሚያዚያ 1 ቀን 2006 ዓ.ም ባካሄደው ቃለ ጉባኤ በፃፈው ደብዳቤ ለሦስት ወር በወር ብር 5,340.00 እና ቶፕአፕ በወር 3,000.00 እየተከፈለ ከሚያዚያ 1 ቀን 2006 ዓ.ም ጀምሮ የተቀጠሩ ሲሆን፣
   - የካቲት 20 2009 ዓ.ም በቁጥር ፕ/ሰ/ሀ/ል/ሚ/ሰሀ/ሰ41/8 የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ከጥር 1 2009 ዓ.ም ጀምሮ ለመንግስት መስሪያ ቤቶች የደመወዝ ስኬል ማስተካከያ እንዲደረግ በተወሰነው መሰረት ከብር 9,507.00 ወደ 10,567.00 በማሳደግ ከየካቲት እስከ ሚያዝያ በድምሩ ብር 31,701.00 (10,567.00*3) የተከፈለ መሆኑን፡-
   - ሠራተኛዋ የደመወዝ ጭማሪ ካልተደረገ እንደሚለቁ በመግለፃቸው ግንቦት 1 ቀን 2009 ዓ.ም የስራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን ጥናት ፕሮጀክት አስተባባሪ በተፃፈ የውስጥ ማስታወሻ ሰኔ 07 ቀን 2009 ዓ.ም በቁጥር ፕ/ሰ/ሀ/ል/ሚ/ሰሀ/ሰ41/10 በተፃፈ ደብዳቤ

መሰረት ከብር 10,567.00 ወደ 11,720.00 በማሳደግ ከግንቦት እስከ ሰኔ በድምሩ ብር 23,440.00 (11,720.00*2) የተከፈለ መሆኑን፣

በድምሩ ብር 55,141.00 ባልተፈቀደ መደብ፣ ባልተያዘና ባልፀደቀ በጀት ያለአግባብ ተከፍሏል፡፡

በጠቅላላው ብር 133,849.00 ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ባልተፈቀደ መደብ፣ ባልተያዘና ባልፀደቀ በጀት ያለአግባብ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

1.5.2 <u>በኦዲቱ ወቅት የተሰጠ ምላሽ</u>፣

በሥራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን ፕሮጀክት በጊዚያዊ በኮንትራት የተፈፀመውን ቅጥር አስመልክቶ በኦዲት ግኝት ላይ በአደረጃጀት የሥራ ምዘናና የክፍያ ጥናት ቢሮ በኩል መልስ እንዲሰጥ በ22/02/2010 ዓ/ም የተፃፈ ማስታወሻ ደርሶን ተመልክተናል፡፡ከዚህ መሠረት፡-

1ኛ/ በፕሮጀክት ጽ/ቤቱ የኮንትራት የሥራ መደቦች እንዲፈቀዱ ተቋሙ በቁጥር ሲሰሚ/10/4/60 በቀን 25/07/2006 ዓ/ም እና በቁጥር ፐ/ሰ/ሚ/10/4/90 በ24/1/2009 ዓ/ም ለአደረጃጀት የሥራ ምዘናና ክፍያ ጥናት ዳይሬክቶሬት ባቀረበው ጥያቄ መሠረት ዳይሬክቶሬቱ በተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት መሠረት ተገቢውን ጥናት አድርጐ በቁጥር ሲ.ሰ.ሚ20/ጠ48/18/378/90 በ3/08/2006 ዓ/ም እና በቁጥር ፐ/ሰ/ሀ/ል/ሚ/10/4/90/2009 በ24/1/2009 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ ተገቢውን ምላሽ ሰጥቷል የተጠቀሱ ደብዳቤዎች ከዚህ ጋር ተያይዞ ቀርቦል፡፡

ከዚህ ውጭ በተፈቀዱ የሥራ መደቦች ላይ የሰው ሃብት የማስማራት /ቅጥር፣ ዕድገት፣ ዝውውር ወዘተ…/ ተግባር የማከናወን ሥልጣንና ኃላፊነት የሰው ሃብት አስተዳደርና ልማት ዳይሬክቶሬት ስለሆነ የቅጥር አፈፃፀም አስመልክቶ መልስ መስጠት ያለበት ይኸው ዳይሬክቶሬት ስለሆነ ጥያቄውን ወደዚያው ማቅረብና ተገቢውን መልስ ማግኘት የሚገባ መሆኑን እንገልፃለሁ፡

1.5.3 <u>ስጋት</u>፣

በአዋጁ ከተሰጠ ስልጣን ከሚፈቅደው ውጪ መስራት መንግስት ያወጣውን ህግና ደንብ ተፈፃሚ እንዳይሆንና ህጎች እንዲጣሱ መንገድ ሊከፍት ይችላል፡፡

1.5.4 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>፣

ሰራተኛው ደመወዝ ካልተጨመረ እንደማይሰራ በመግለፁ ብቻ በቃለ ጉባኤ የደመወዝ ማስተካከያ ማድረግና ባልተፈቀደ መደብ፣ ባልተያዘና ባልፀደቀ በጀት ክፍያ መፈፀም ትክክለኛ አሰራር ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የሥራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን ፕሮጀክት ከጠቅላይ

ሚኒስትር ጽ/ቤት መዋቅሩ ፀድቆ ባልመጣ በቁጥር ፐ/ሰ/ሀ/ል/ሚ/10/4/90/2009 በ24/1/2009 ዓ/ም ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ዳይሬክቶሬት ማለትም ለአደረጃጀት የሥራ ምዘናና ክፍያ ጥናት ዳይሬክቶሬት በተፃፈ ደብዳቤ ተገቢውን ምላሽ መሰረት የተስተካከለ መሆኑን ምላሽ ቢሰጥም ትክክለና አሰራር ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑ በኮንትራት ሰራተኛ እንዲቀጠር አስፈላጊ ከሆነ መጠየቅ ሲቻል ካለመዋቅር እና በሌለ በጀት ቅጥር መፈፀም ትክክለኛ አሰራር አይደለም፡፡ በመሆኑም የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድና እንዲከፈል መደረግ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም መሰል ስህተት እንዳይፈጸም ቁጥጥር እና ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

1.6.1 <u>**ግኝት፣አለአግባብ የተከፈለ የትራንስፖርት ሂሳብ፣**</u>

ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በቁጥር ሲ.ሰ.ሚ.30/ጠ13/40/883 ቀን 29/10/04 የመንግስት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል አከፋፈል መመሪያ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 3 "በሥራ ባህሪያቸው አስገዳጅነት ከማዕከልና ከክልል ተልከው ረዘም ላለ ጊዜ በመስክ ሥራ ከመደበኛ የሥራ ቦታቸው በመራቅ ከ3 ወር በላይ ለሚቆዩ የመንግስት ሠራተኞች ሥራውን በቋሚነት /በጊዜያዊነት ባለሙያ መድቦ ማሠራት የማይችል መሆኑ በመሥሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊ ከታመነበት እና በጀት አስቀድሞ መያዙ ሲረጋገጥ የተቋሙ የበላይ ኃላፊ ሥራው እስኪጠናቀቅ ላለው ተጨማሪ ጊዜ የቀን ውሎ አበል ሊፈቅድ ይችላል፡፡" የሚለውን በሚኒስቴር መ/ቤቱ ስለመፈፀሙ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ የስራ ምዘናና ደረጃ አወሳሰን ጥናት ፕሮጀክት (JEG) አባላት ወደ መጡበት ክልል ለበዓላት ሲሄዱ ከመንግስት በጀት ለትራንስፖርት በድምሩ ብር 74,424.00 ያለአግባብ የተከፈለ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡**ዝርዝሩ በአባሪ-1 ቀርቧል፡፡**

1.6.2 <u>**በኦዲቱ ወቅት የተሰጠ ምላሽ**</u>**፣**

ምላሽ አልተሰጠም፡፡

1.6.3 <u>**ስጋት፣**</u>

ከመመሪያና ደንብ ውጭ ክፍያዎችን መፈፀም የመንግስት ውስን በጀት አላግባብ ወጪ እንዲሆን መንገድ የሚከፍት አሠራር ከመሆኑም በተጨማሪ መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ ሊዳርግ ይችላል፡፡

1.6.4<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከተለያዩ ክልሎች ወደ አዲስ አበባ ለመጡ ባለሞያዎች በየቀኑ የውሎ አበል እየከፈለ በየበዓሉ ወደ ቤተሰቦቻቸው ሲሔዱ የሚከፈለው የትራንስፖርት አበል ትክክል አይደለም፡፡ በ2008 ዓ.ም የፌደራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት የኦዲት ግኝት ላይ ይህ ሀሳብ ተነስቶ ለስራ እንጂ ቤተሰብ ለመጠየቅ አለመሆኑን እና ይህ አሰራር እንደተስተካከለ ቢገለፅም፣ የእርምት እርምጃ አለመወሰዱን ተረጋግጧል፡፡ አሁንም ስራ አመራሩ ያስፈልጋል ብሎ የሚያምን ከሆነ ፕሮጀክቱን ያፀደቀውን አካል ማስፈቀድ ካልሆነ ግን ማስተካከያ እንዲያደርግ በድጋሚ እንገልፃለን፡፡ የተከፈለውም ብር 74,424.00 እንዲከፈል መደረግ ይኖርበታል፡፡ የግዥ ፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክተር ክፍያ ሲፈፅም በመንግስት ህግ ብቻ መሆን ይገባዋል፡፡

1.7.1 <u>ግኝት፣ ከተፈቀደወ መዋቅር ውጭ ተከፍሎ የተገኘ፣</u>

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በ23/09/2005 ዓ.ም በቁጥር ሲሰሚ30/ጠ532/1/11 ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት የተቀናጀ የሲቪል ሰርቪስ መረጃ አያያዝ ስርዓት /ICMIS/ ፕሮጀክት እንዲተገበር ባቀረበው መዋቅር መሰረት በ27/12/2005 ዓ.ም በቁጥር መ80-963-10 የቀረበውን ጥናት አፅድቆ መላኩ በድጋሚ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አዲስ አሻሽሎ የላከው መዋቅር በቀን 17/06/2009 ዓ.ም በቁጥር መ80-813/7 ፀድቆ መላኩ ይታወቃል፡፡ በዚሁ መሰረት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ስለመስራቱ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በኮንትራት ማለትም በፕሮጀክቱ ወይም በመደበኛው ሳይሆን በሁለቱም መዋቅር እያስተናገደ መሆኑን ተመልክተናል፡፡

- ይህም በመሆኑ በልዩነት በእያንዳንዱ ሰራተኛ ላይ ከታች የተዘረዘረው ልዩነት የሚታይ ሲሆን በጠቅላላ ድምር ብር 102,779.80 ያላግባብ ከተፈቀደለት መዋቅር ውጭ ከፍሎ ተገኝቷል፡፡
- እንዲሁም የፕሮጀክት ማናጀር እና ምክትል ማናጀር በኮንትራት ሠራተኞች ማሰራት ሲኖርበት በቋሚ ሰራተኞች እያሰራ መሆኑን እና እንደዚሁም ምክትል ማናጀር ባልተተከለ ደመወዝ ክፍያ እየተፈፀመ መሆኑን በኦዲታችን ወቅት አረጋግጠናል፡፡ ዝርዝሩ ቀጥሎ ቀርቧል፡-

የሰራተኛኛስም	የስራድርሻ	የተፈቀደ ደሞዝ መጠን		ሚ/መ/ቤቱየ ጨመረው	ወርብዛት	ልዩነት
		ደሞዝ	ትራንስፖርት			

ዶ/ር ጌታቸው መለሰ ደሣለኝ	ፕሮጀክት ማናጀር	14,000.00 በአሁኑ 21,000.00	3,000.00 በአሁኑ 4,000.00	15,960.00	30	58,800.00
		14,000.00	3,000.00	17,036.00	3	9,108.00
	ጠቅላላ ድምር ብር					**67,908.00**
አቶሚኒሊክአሰ ፋአርምዲ	ኔትወርክአ ድሚኒስትሬ ተር	12,000.00 በአሁኑ 17,000.00	1,000.00 በአሁኑ 3,000.00	12,809.00	3	**2,427.00**
አቶአብይዋለል ኝአዳል	ኔትወርክአ ድሚኒስትሬ ተር	12,000.00 በአሁኑ 15,000.00	1,000.00 በአሁኑ 2,000.00	12,809.00	3	**2,427.00**
አቶአሸንፊበላ ይይመር	በሰውሀብት መረጃባለሞ ያ	8,000.00 በአሁኑ 15,000.00	500.00 በአሁኑ 2,000.00	9,920.00	3	**5,760.00**
አቶስንታየሁቦ ያሞኢዴቦ	በዳታአሰባሰ ብናምዝገባ አስተዳደር	7,000.00 በአሁኑ 12,000.00	500.00 በአሁኑ 1,500.00	8,750.00	3	**5,250.00**
አቶአረጋዊአፅ ባሃሕሸ	ዳታኢንኮደ ር	2,514.00 በአሁኑ 5,000.00	0 በአሁኑ 500.00	2,872.00	6	2,148.00
		2,514.00	0	4,085.00	3	4,713.00
		ጠቅላላ ድምር ብር				**22,725.00**
አቶአቤልሚሊ ዮንአለሙ	ዳታኢንኮደ ር	2,514.00በ አሁኑ 5,000.00	0 በአሁኑ 500.00	2,872.00	6	2,148.00
		2,514.00	0	4,085.00	3	4,713.00
		ጠቅላላ ድምር ብር				**6,861.00**
ወ/ሪትሮዳስነጋ ተገኝ	ዳታኢንኮደ ር - ከህዳር 7/2009 ጀምሮ	2,514.00 በአሁኑ 5,000.00	0 በአሁኑ 500.00	2,872.00	2	572.80
		2-514.00	0	4,085.00	3	4,713.00
		ጠቅላላ ድምር ብር				**5,285.80**
		ጠቅላላ ድምር				**102,779.80**

1.7.2 <u>በኦዲቱ ወቅት የተሰጠ ምላሽ፣</u>

ስለፕሮጀክቱየቀረበውንየኦዲትመግለጫሪፖርትአንድበአንድየተመለከትንሲሆንበሥራላይባሉመ መሪያዎችመሠረትሪፖርቱሲፈተሽየግኝትመግለጫውአግባብያላቸውመመሪያዎችንያገናዘበሆኖአ ላገኘነውም፡፡በዚህምመሰረት፡-

1. በመንግሥትመሥሪያቤቶችሥርበሚኖሩፕሮጀክቶችውስጥእንደሙያውአስፈላጊነትቋሚሠራት ኛውንበማዛወርወይምጊዜያዊሠራተኛበመቅጠርማሠራትየሚቻልስለሆነ፣የፕሮጀክቱማናጀርእና ምክትልየሥራመደቦችበኮንትራትሠራተኞችመሸፈንሲገባውቋሚሠራተኛእንዲመደቡበትመደ

ረጉአግባብአለመሆኑንበመግለጽስህተቱእንዲስተካከልበማለትየቀረበውንአስተያየትበተመለከተ በፌዴራልመንግሥትመ/ቤቶችየጊዜያዊሠራተኞችቅጥርአፈፃፀምመመሪያክፍልሦስትመሠረት ለፕሮጀክቱሥራቋሚሠራተኞችየሚመደቡበትንሥርዓትተከትሎበፕሮጀክቱየአመራርነትቦታላ ይብቃትያላቸውንየሥራኃላፊዎችመመደብየከፍተኛአመራሩኃላፊነትበመሆኑበዚህአግባባየተፈ ጸመውምደባየህግ/የአሠራርስህተትየለውም፡፡ (መመሪያውፎቶኮፒአባሪተደርጓ)

2. ባልተፈቀደመዋቅርክፍያተፈጽሟልበሚልየቀረበውንአስተያየትበተመለከተየፕሮጀክትጽ/ቤቱ መዋቅርበጥናቱተደግፎለጠቅላይሚኒስትርጽ/ቤትውሣኔእንዲሰጥበትከተላከበኋላየጠቅላይሚኒስ ትርጽ/ቤትነሐሴ 27/ ቀን 2005 ዓ.ምበቁጥርመ-80-963/10 እናበቁጥርመ80-813/7 በ17/06/2009 ዓ.ምበተፃፈደብዳቤአደረጃጀቱንናየደመወዝስኬልናጥቅማጥቅሙንተግባራዊእንዲደረግየፈቀደ መሆንባልተፈቀደመዋቅርየተፈጸመየሰውሃብትስምሪትአለመኖሩንእንግልፃለን፡፡ (ከጠቅላይሚኒስቴርየተፈቀደበትእናመዋቅርፎቶኮፒአባሪተደረጓል)

1.7.3 <u>ስጋት፤</u>

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከህግና ከደንብ ውጭ መስራቱ የህግ ክፍተት እንዲፈፀም ሊያደርግ እና ውስን የመንግስት ሀብት እንዲባክን መስመር ሊከፍት ይችላል፡፡

1.7.4 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

በተሰጠው ምላሽ መሠረት ቋሚ ሠራተኛ ወደ ፕሮጀክት ማስታወቂያ አውጥቶ በማወዳደር በማዛወር መሥራት ይችላል፡፡ ይሁንና የቋሚ መደብ ሥራውን በመልቀቅ በኮንትራት (በጊዜያዊነት) ሊሠረ ይገባል፡፡ በመመሪያው መሠረት በኮንትራት ቅጥር መፈጸም ያለበት ሠራተኞችን በማወዳደር ሊዛወር እንደሚችል ግንዛቤ ሊወሰድ ይገባል፡፡ በመሆኑም ያለአግባብ ከተፈቀደለት መዋቅር ውጭ የተከፈለውን በብልጫ ብር 102,779.80 እንዲከፈል አለበት፡፡ ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ጠይቆ የተፈቀደለትን መዋቀቅር መሰረት ብቻ አድርጎ መስራት ይጠበቅበታል፡፡ ይህን የፈቀደ አካልም ተጠያቂ መሆን ይኖርበታል፡፡

መዋቅሩ በሚፈቅደው መሰረት በኮንትራት ሰራተኞች ማሰራት ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እንደዚህ ያለ ስህተት እንዳይፈፀም ያሉትን መረጃዎች በትክክል ማገናዘብ ይኖርበታል፡፡

1.8.1 **ግኝት፣የሲቪል ሰርቪስ መረጃ አያያዝ ስርዓት ሲስተም መስራቱ ሳይረጋገጥ በየጊዜው ክፍያ መከፈሉን /ICMIS/ በሚመለከት፣**

የኢትዮጵያ ፌደራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 ክፍል አንድ አንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 8 ላይ "ወጪ" ማለት የመንግስት መ/ቤቶች በገቡት ውል ወይም ባለባቸው የክፍያ ግዴታ መሰረት ከተፈቀደላቸው በጀት ላይ ገንዘቡን የመቀበል መብት ላላቸው ሰው ወይም ድርጅት ወጪ አድርጎ መክፈል መሆኑን ይገልፃል፡፡ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ወጪ ከመደረጉ በፊት ለክልሎች የተቀናጀ የሲቪል ሰርቪስ መረጃ አያያዝ ስርዓት ፕሮጀክት /ICMIS/ ለመተግበር ከኢትዮጵያ ቴሌኮምኒኬሽን መ/ቤት ጋር በገባው ውል መሰረት የሲቪል ሰርቪስ የሰው ሀብት አመራር መረጃዎች ሥርዓት በወጥነት እንዲዳብርና እንዲተገበር ለማድረግ ማዕከላዊ መረጃ ምንጭ ሆኖ ማገልገል አንዱ በመሆኑ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በመደገፍ ጥራቱን የተጠበቀና ወቅታዊ መረጃዎችን ከክልሎች ጋር በመጣመር ለጀመረው ዝርጋታ እየሰራ መሆኑን ሳያረጋጋጥ፣ በአማራ፣ በደቡብ እና በኦሮሚያ በየወሩ በገባው ውል ብቻ መሰረት በማድረግ የተቀናጀ የሲቪል ሰርቪስ መረጃ አያያዝ ስርዓት ስለመስራቱ ሳያረጋግጥ በድምሩ ብር 1,032,637.58 በ2009 በጀት ዓመት ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ **ዝርዝሩ በአባሪ-2 ቀርቧል፡፡**

1.8.2 **በኦዲቱ ወቅት የተሰጠ ምላሽ፣**

በሚ/ር መ/ቤታችን እየተተገበረ ስላለው የተቀናጀ የሲ.ሰ. መረጃ አያያዝ ስርዓት የአገራችንን የሰው ሀብት መረጃ አያያዝ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እንዲደገፉና ከቅጥር እስከ ስንብት ያሉ ክንውኖችን በስርአቱ ታግዘው እንዲከናወኑ አሰራሩም ቀላልና ቀልጣፋ የመረጃና አገልግሎት አሰጣጡም ተደራሽ ለማድረግ ለተገልጋይ እርካታን ለማረጋገጥ ሲባል በርካታ ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡ ስለዚህም ስርአቱ ከሚተገበርባቸው የፌደራልና ክልል ተቋማት የመሠረት ልማት ሁኔታ እየታየ በተለይ የክልል የፐፐሊክ ሰርቪስ ተቋማት የተለያዩ ድጋፎች በፕሮጀክት ፅ/ቤቱ በኩል ይደረግላቸዋል፡፡ ለምሳሌ የኮምፒውተርና ተዛማጅ እቃዎች ስርጭት፤ በወረዳኔት መስመር እንዲዘረጋላቸው ማድረግ፤ ከሚገነባው የዳታ ማዕከል ጋር በኔትወርክ ማስተሳሰር ወዘተ.. መጥቀስ ይቻላል፡፡

በመሆኑም ወደዚህ ስርአት የሚካተቱ ተቋማት እንደተለዩ 3ዙር የመረጃ አያያዝና የሲስተም አጠቃቀም ስልጠና እየተከናወነ ጎን ለጎን ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር በመዋዋል የወረዳ ኔት መስመር ይዘርጋላቸዋል፡፡ ይህ መስመር ከድጋፍና ክትትል በኃላ ተቋማቱ ወደ ሙሉ ትግበራ ሲገቡ ከላይ የተጠቀሰውን ሂደት ኦንላይን ማከናወን ይጀምራሉ መረጃቸውም በተማከለ ሁኔታ በማዕከሉ

እንዲቀመጥ ይደረጋል። እስከዚያውም ድረስ ግን ኢሜል ለመላክ፤ ኢንተርኔት፤ ለመጠቀም የመስመር ላይ ድጋፍ እንዲያገኙ ወዘተ.. ያግዛቸዋል።

በመሆኑም ቀድሞ የወረዳኔት ያልተዘረጋለቸው ተቋማት በተለይ በአብዛኛው የአማራና፤ ደበቡ ብ/በ/ክልል ሲሆኑ ከዚህ በፊት በአደረጃጀታችው ምክንያት የወረዳኔት መስመር የነበራቸውን ክልሎች አ.አ አስተዳደር፤ኦሮሚያና ትግራይ ክልሎች ናቸው መስመሩ ለትግበራው ወሣኝ ስለሆነ የዋናው ኦዲተር መስራቤት ኦዲተሮች ሁሉንም ተቋም ኦዲት አድርጎ መስመሩን እየተጠቀሙበት ስለመሆናቸው ሳይረጋገጥ የተወሰኑ ተቋማት ወደ ትግበራ አልገቡም በሚል ወይም የወረዳኔት መስመሩ ለጊዜው ተቋርጦ አግኝተናል በሚል ወይም በሌላ ምክንያት ክፍያው እንዲቆም ሀሳብ መስጠታቸው ተቋማቱ ከፕሮጀክቱ እንዳይጠቀሙ ይደረግ ወይም በሌላ አነጋገር የተወሰኑ ክልሎች ከዚህ በፊት የወረዳኔት መስመር ያላቸው ብቻ ያለፈታዊነት አገልግሎቱን ያግኙ ወይም የወረዳ ኔት መስመር የሌላቸው ወደ ስርአቱ አይካተቱም ማለት ስለሆነ ወይም ፕ/ት ፅ/ቤቱ ስራ ያቁም እንደማለት ስለሆነ እንደገና እንዲጤን እንጠይቃለን። በሌላ በኩል አንድ ተቋም የወረዳ ኔት መስመር ሲቋረጥ ለመከታተል እንዲቻል የኔትወርክ ሞኒተሪን ሶፍትዌር በመጠቀም ችግር ሲያጋጥም ኢትዮ ቴሌኮም በማስመዝገብ ጥገና እንዲደረግ የሚያስችል አሰራር ስላለን ወደ ሙሉ ትግበራ እስኪገቡ ድረስም የመስመር ላይ ድጋፍና ክትትል ለማድረግ የወረዳ ኔት መስመር ቀድሞ መዘርጋት የመረጃ ስርአት ትግበራው አንዱ የማይታለፍ ቅድመ ሁኔታ መሆኑም ጭምር እንዲታወቅ እንላለን።

1.8.3 <u>ስጋት፣</u>

የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ የአገልግሎት ክፍያ መፈጸም ውስን የመንግስት ሀብት እንዲባክን መስመር ሊከፍት ይችላል፡፡

1.8.4 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የዘረጋውን የመረጃ ሥርዓቱ በሥራ ላይ ስለ መተግበሩ በዋና ኦዲተር መ/ቤቶች በተደረገው ምልከታ ከአንድ ወረዳ ብቻ እሱም በቂ ባልሆነበት ክሎት እገዛና ድጋፍ በበቂ ሆኔታ ባልተደረገበትና ባለድርሻ አካላትም ባላሳተፈበት በገባው ውል ብቻ አገልግሎት ክፍያ መፈፀሙ ትክክለኛ አሰራር አይደለም፡፡ በመሆኑም ቴክኖሎጂውን በመደገፍ ጥራቱን የተጠበቀና የታለመለትን አላማ እንዲያሳካ ድጋፍና ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡ የስራ አመራሩም ከመንግስት ቋት ወጪ በመሆን የሚተገበር ፕሮጀክት በመሆኑ በየግዜው ትክክል እና ድጋፍ ሊደረግ ይገባል እንላለን፡፡

1.9.1 <u>ግኝት፣የጥናት ግዥ በሚመለከት፣</u>

የፌዴራል መንግስት የግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ 649/2001 ምዕራፍ 1 አንቀጽ 3 ስለተፈፃሚነት ወሰን ንዑስ አንቀጽ 2 "ለ" "የመንግስት መሥራያ ቤቶች ዕቃዎችን፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎችን፣ የምክርና ሌሎች አገልግሎቶችን ወጪ በመሸፈን ከሌሎች የመንግስት መሥራያ ቤቶች ለማግኘት በሚያደርጉት ውል ላይ የግዥ አዋጁ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡" የሚል ሲሆን ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ቀጥታ "ለአገር አቀፍ የዜጎች እርካታ ዳሰሳ ጥናት" ከኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የወጪ ማስመስከሪያ 12083 በ15/09/2009 ብር 2,071,152.94 እና የወጪ ማስመስከሪያ 12453 በ23/10/2009 ብር 3,451,921.57 በድምሩ ብር 6,903,843.14 የጥናት ግዥ የፈፀመ ሲሆን፡-

- ውል የገባውም ከኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ጋር ቢሆን ኖሮ ዩኒቨርሲቲው በገቢ የሂሳብ መደብ 1489 (ልዩ ልዩ ገቢዎች) መመዝገብ ሲገባው 5054 ሌሎች የመያዣ ሂሳቦች (Other Deposits) መመዝገቡን በሠነድ የተመለከትን መሆኑ፡-
- እንዲሁም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በውሉ ክፍያ የሚፈፀመው በየስራው እንቅስቃሴ መሆኑን ቢደነግግም ከውል ጊዜው ውጭ በመብለጥ ክፍያ የፈጸመው መሆኑን በኦዲት ወቅት አረጋግጠናል፡፡

1.9.2 <u>በኦዲቱ ወቅት የተሰጠ ምላሽ፣</u>

መልስ አልተሰጠም፡፡

1.9.3 <u>ስጋት</u>፣

አዋጁ ከመንግስት መሥራያ ቤቶች ወደ መንግስት መስሪያ ቤቶች የቀጥታ ግዥ ተፈፃሚ እንዲሆን ቢደነገግም በገቢ ያለመመዝገቡ የመንግሥት ገንዘብ ወደ ግለሰቦች ኪስ ያላግባብ ሊገባ ይችላል፡፡

1.9.4 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በትክክል ከኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ጋር ውል መዋዋሉን ማረጋገጥ አለበት፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ስለወጪው ማረጋገጫ የቀረበው ደረሰኝ ለዩኒቨርሲቲው ገቢ ስለመሆኑ የቀረበ ማረጋገጫ መሆን ነበረበት፡፡
- ጥናቱ በተቀመጠው አቅጣጫ ክፍያው መፈፀም ነበረበት፡፡ ቀድሞ ከውል ጊዜው በፊት ክፍያ መከፈሉ ትክክለኛ አሰራር አይደለም፡፡ ለወደፊቱም ማንኛም ግዥ ሲፈጸም ከመንግስት ተቋም ከሆነ ገቢው በገቢ ደረሰኝ የተመዘገበ ማረጋገጫ መቀበል ያስፈልጋል፡፡ የስራ አመራሩ ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

1.10.1 ግኝት፣አለአግባብ የተፈጸመ የቀጥታ ግዥ፣

የፌዴራል መንግስት የግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ 649/2001 አንቀጽ 33 የግዥ ዘዴዎች ንዑስ አንቀጽ 2 "የመንግስት መስሪያ ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግልፅ የጨረታ ዘዴ መፈፀም አለባቸው።" ንዑስ አንቀጽ-3 "የመንግስት መስሪያ ቤቶች ከግልፅ ጨረታ ውጭ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ግዥ መፈፀም የሚችሉት በዚህ አዋጅ የተገለፁት ሁኔታዎች ከተሟሉ ብቻ ይሆናል።" እንዲሁም አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ- ሰ “የመንግስት ንብረት ኢኮኖሚያዊ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ አገልግሎት ላይ መዋሉን ያረጋግጣል።” የሚል ሲሆን ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ግዥዎችን በግዥ ዘዴ መፈፀሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ስናደርግ፡-

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በ26/05/2009 ዓ.ም የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 11138 ብር 11,960.00 ለብሄር ብሄረሰቦች ቀን በዓል የባጅ ግዥ እንዲፈፀም በተጠየቀው መሰረት ያለ ዋጋ ማወዳደሪያ ወይም በቀጥታ ግዥ ከጂቲ ማተሚያ ቤት 400*29.90= ብር 11,960.00 ክፍያ የተፈፀመ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡
- በተለያየ ቀንና የደረሰኝ ቁጥር ያለምንም ውድድር ከተለያዩ አቅራቢ ድርጅቶች በድምሩ ብር 421,687.96 በቀጥታ ግዥ መፈፀሙን ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝሩ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	አቅራቢድርጅትስም	የደረሰኝቁጥር	ቀን	የተገዛውግዥ	የገንዘብመጠን
1	ምንአየኃላ/የግ/ኩባንያ	BPV-10499	30/2/09	የፈርኒቸርግዥ	191,849.99
2	ዳንኤልሙሉአጠቃላይአስመጪ	BPV-11119	18/02/09	የሞባይልቀፎግዥ	85,100.00
3	ትርኢኖቫአትሬድንግ -PLC	BPV-10459	29/02/09	ላፕቶፕግዥ	20,700.00
4	ሙሀጅርነጋሽየህንፃመሣሪያዎችመደብር	BPV-11058	08/05/09	ካዝናግዥ	41,200.00
5	ናሽናልማርኬተርስኃ.የተ.የግ.ማህበር	BPV-10637	15/3/09	ፕሪንተርግዥ	52,937.97
6	አመሀመዝገቡስልክየሞባይልቀፎናየመገናኛመሳሪያዎችችርቻሮንግድ	BPV-10503	30/02/09	IPAD ግዥ	29,900 ለክቡር አቶ ዛዲግ አብረሃ
ጠቅላላ ድምር ብር					421,687.96

1.10.2 <u>በኦዲቱ ወቅት የተሰጠ ምላሽ</u>፣

መልስ አልተሰጠም፡፡

1.10.3 <u>ስጋት</u>፣

በግዥ መመሪያ መሠረት ግዥው ካልተፈፀመ በግዥ አፈፃፀም ረገድ የመንግስት ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ሊያሳጣና የመንግሥት ገንዘብ ወደ ግለሰቦች ኪስ ያላግባብ ሊገባ ይችላል፡፡

1.10.4 <u>የማሻሻያሀሳብ</u>፣

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ማንኛውንም ግዥ ሲፈፅም በአዋጁ እና አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው መመሪያ መሰረት በተገለጹት የግዥ ዘዴዎች ብቻ መሆን አለበት፡፡ ለወደፊቱም ማንኛም ግዥ ሲፈጸም ወድድርን መሰረት ያደረገ እንዲሆን የስራ አመራሩ ጥብቅ ቁጥጥር በማድረግ የመንግስት ግዥ በዕቅድ ላይ የተመሰረተ እና በአዋጁ የተመለከቱ የግዥ መርሆዎችን የጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

1.11.1 <u>ግኝት</u>፣ <u>ዝቅተኛ ዋጋ አቅራቢ እያለ ከከፍተኛ አቅራቢ የተገዛ</u>፣

ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቀን 30/02/2009 ዓ.ም የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 10441 ብር 169,648.00 የቀን መቁጠሪያ /Calender/ ህትመት ግዥ በዋጋ ማቅረቢያ በተሰጠው ውድድር ሲደረግ፣ ካቀረቡት ሦስት ድርጅቶች ውስጥ ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበው አፕል ማተሚያ ቤት ኃ/የተ/የግ/ማህበር 2000*40.25= ብር 80,500.00 ሆኖ ሳለ፣ ያለአግባብ ከጃጃው አታሚዎችና ዴቨሎፐርስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር 2000*84.82= ብር 169,640.00 በመግዛቱ በብር 89,140.00 ያለአግባብ የከፈለ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

1.11.2 <u>በኦዲቱ ወቅት የተሰጠ ምላሽ</u>፣

መልስ አልተሰጠም፡፡

1.11.3 <u>ስጋት</u>፣

ከመንግስት ውስን ሀብት የሚመጣ በጀት በአግባቡና ወጪ ቆጣቢ በሆነ አሰራር ተግባራዊ ካልተደረገ የመንግስት ሀብት ለብክነትና ለመዝበራ ሊጋለጥ ይችላል፡፡

1.11.4 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>፣

ግዢዎች በፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ መሰረት መከናወን ይኖርበታል፡፡ ከተቀመጠው አዋጁ፣ ደንብ፣ መመሪያ ውጪ ማካሄድ ስለማይቻል ለወደፊቱ መመሪያ በማገናዘብ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

1.12. ግኝት፣ ተቆራርጦ በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ የተፈጸመ፣

የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በታህሳስ 12 ቀን 2008 ዓ.ም የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ እንደገና ለማሻሻል የወጣ መመሪያ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 24.2 "ለግንባታ ሥራ እስከ ብር 500,000.00፣ ለዕቃ እስከ ብር 200,000.00፣ ለምክር አገልግሎት እስከ ብር120,000.00 እና ለሌሎች አገልግሎቶች እስከ ብር150,000.00 ከዚህ የገንዘብ መጠን የማይበልጥ እና በዋጋ በማቅረቢያ የግዥ ዘዴ የሚፈፀም ግዥን ለግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ማቅረብ ሳያስፈልግ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ወይም እርሱ በሚወክለው ሰው እንዲፀድቅ በማድረግ ግዥ መፈፀም ይችላል፡፡" ይላል፡፡ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በዚህ መሰረት ስለመስራቱ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በጨረታ ግዥ መፈጸም ሲገባው፣ ከተለያዩ አቅራቢዎች ቆራርጦ በዋጋ ማቅረቢያ በአጠቃላይ ብር 10,013,266.63 ግዥ መፈፀሙን ተረጋግጧል፡፡ **ዝርዝሩ ቀጥሎ ቀርቧል።**

ተ.ቁ	አቅራቢድርጅትስም	የደረሰኝ ቁጥር	ቀን	ምክንያት	የገንዘብመጠን
1	ሪፍትቫሊሆቴል	PV-11624	19/7/09	በዋጋማቅረቢያ	1,828,579.70
2	ሲዮናትሆቴል	PV-10972	20/04/09	/ICMIS/ የመኝታ፣የመስተንግዶ	2,359,413.65
3	ኤክስኪዩቲቭሆቴል	PV-11655	29/02/09	ከመንግስትከፍተኛአመራሮችጋርወይይት	1,366,715.06
4	ኤክስኪዩቲቭሆቴል	PV-10581	13/03/09	የገጠርልማትክትትልናድጋትየስልጠናመድረክ	372,283.18
5	ኤክስኪዩቲቭሆቴል	PV-10146	11/02/209	በዋጋማቅረቢያ	344,730.21
6	ኤክስኪዩቲቭሆቴል	PV-10450	30/02/09	JEG የሥልጠንመድረክ	246,585.19
7	አዘመንሆቴል	PV-10494	06/03/09	የ2009 ዕቅድውይይት	351,632.61
8	ፒራሚድሆቴል	PV-09641	10/12/08	መልካምአስተዳደርመድረክውይይት	450,288.46
9	ሶደሬሪሶርትሆቴል	PV-11941	02/09/09	ለተወካዮችምክርቤትአባላትየመኝታእናየመስተንግዶግዥ	397,980.11

10	ሃፀይዮሀንስሆቴል	PV-12160	24/09/09	የተቀናጀየሲቪል ሰርቪስመረጃአያያዝስርዓት /ICMIS/ የመኝታ፣የመስተንግዶእናየአበልክፍያ	259,738.00
11	ቶፕቴንሆቴል	PV-12431	22/10/09		2,035,320.46
ጠቅላላድምር					7,320,228.06

1.12.2 በኦዲቱ ወቅት የተሰጠ ምላሽ፣

መልስ አልተሰጠም፡፡

1.12.3 ስጋት፣

በግዥ መመሪያ መሠረት ግዥው ካልተፈፀመ በግዥ አፈፃፀም ረገድ የመንግስት ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ላያስገኝ ይችላል፡፡ እንዲሁም የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ ወጪ ሊሆን ይችላል፡፡

1.12.4 የማሻሻያሀሳብ፣

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ማንኛውንም ግዥ ሲፈፅም በአዋጁ እና አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው መመሪያ መሰረት በተገለጹት የግዥ ዘዴዎች መሠረት በውድድር መሆን አለበት፡፡ ለወደፊቱም ማንኛም ግዥ ሲፈጸም ወድድርን መሰረት ያደረገ እንዲሆን የስራ አመራሩ ጥብቅ ቁጥጥር በማድረግ የመንግስት ግዥ በዕቅድ ላይ የተመሰረተ እና በአዋጁ የተመለከቱ የግዥ መርሆዎችን የጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

1.13.1 ግኝት፣የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ክፍያ የተፈጸመ፣

የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 9 ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ሊደረጉ የሚገቡ ጥንቃቄዎች በሚለው ስር አንቀጽ ንዑስ 7 ለተገዛ ዕቃ ወይም አገልግሎት ሂሳብ ማወራረጃ በማስረጃነት መቅረብ ያለበት ዋናው (ኦርጅናል) ደረሰኝ እንደሆነ ይደነግጋል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ግን በተለያየ ቦታ በሚያደርገው የስልጠና እና የስብሰባ መስተንግዶ ወጪ ከማድረጉ በፊት የተሳታፊዎች ዝርዝር፣ ስለመሳተፋቸው የሰዓት መቆጣጠሪያ ማስረጃ እና አበል የተከፈለበትን ዋና ሰነድ ስለመሟላቱ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በድምሩ ብር

11,161,186.19 በፎቶ ኮፒ ማስረጃ ክፍያዎች ተፈፅመው ተገኝተዋል፡፡ ዝርዝሩ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

	አቅራቢድርጅትስም	የወጪማስመስከሪያቁጥር	ቀን	የገንዘብመጠን	የወጣበትምክንያት
1	ኤክስዩቲቭ ሆቴል	PV-10450	30/02/09	246,585.19	ሥራምዘናናየመኝታአገልግሎትግዥ
		PV-10581	13/03/09	372,283.18	የገጠርናአስተዳደርየመኝታእናየመስተንግዶአገልግሎትግዥ
		PV-11655	21/07/09	1,366,715.06	ለፌደራልተቋማትየሠውሀብትአስተዳደርየምክክርመድረክየመኝታእናየመስተንግዶአገልግሎት
2	አዩኢንተርናሽናልሆቴል	PV-10146	11/02/09	344,730.21	አዲስለተቀጠሩሠራተኞችትውውቅየመስተንግዶአገልግሎት
3	ሲዮናትሆቴል	PV-10749	06/04/09	2,208,269.90	የተቀናጀየሲቪልሰርቪስመረጃአያያዝስርዓትከክልልለተወጣጡስልጣኞችየመኝታእናየትራንስፖርትአገልግሎትግዥ
4	የኢትዮጵያ ሥራ አመራር	PV-10516	08/03/09	2,119,259.28	የስራምዘናናደረጃአወሳሰንጥናት JEG) ለስራዝርዝርቀረፃየመኝታእናየመስተንግዶአገልግሎትግዥ
		PV-11733	25/07/09	158,000.60	የአገርአቀፍየሰዉሃብትልማትፖሊሲዝግጅትአብይእናቴክኒክኮሚቴአባላትየመኝታእናየመስተንግዶአገልግሎትግዥ
		PV-11707	22/07/09	2,512,101.94	የስራምዘናናደረጃአወሳሰንጥናት JEG) ወደአዲሱየምዘናስርዓትእንዲገቡለሰልጣኞችየመኝታእናየመስተንግዶአገልግሎትግዥ
		PV-11237	08/06/09	389,900.26	የዜጎችአቅምግንባታየህዝብክንፍለብዙሀንማህበራትስልጠናለመስትየመኝታእናየመስተንግዶአገልግሎትግዥ
		PV-11906	25/08/09	249,880.05	ምንምማስረጃያልተያያዘዶክሜንት
		PV-10126	25/01/09	65,031.50	ፐብሊክስርቪስቀንበዓልአከባባርለዋንጫናሰርትፍኬትለምሳናሻይቡናመስተንግዶግዥ

5	ፒራሚድ ሆቴል እና ሪዞርት	PV-09641	10/12/08	450,288.46	የሪሪፎርም መልካም አስተዳደር ካላስተር ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች የመኝታ እና የመስተንግዶ አገልግሎት ግዥ
		PV-09900	03/01/09	25,124.56	
6	አዘማን ሄቴል	PV-10494	06/03/09	351,632,61	የ2008ዓ.ምበጀትክንውንናየ2009ዓ.ምዕቅድለማድረግ ??
7	አይኢ. ኔትዎርክ ሶሉሽንስ ኃላ/የተ/የግ/ማ	PV-11218	02/06/09	653,016.00	የተቀናጀየሲቪልሰርቪስመረጃአያያዝስርዓትባለሞያለኔትወርክዕቃዎችናሶፍትዌሮችስልጠና
			ጠቅላላ ድምር ብር	11,161,186.19	

1.13.2 <u>በኦዲቱ ወቅት የተሰጠ ምላሽ</u>፣

መልስ አልተሰጠም፡፡

1.13.3 <u>ስጋት</u>፣

ክፍያውም ትክክለኛነት ላያሳይ እና ከተገኘው አገልግሎት በላይ ክፍያ ሊፈፀም ይችላል፡፡

1.13.4 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>፣

የግዥ ፋይናንስ አስተዳደር ዳይሬክተር ክፍያ ሲፈፅም በመንግስት ህግ ብቻ መሆን አለበት፡፡ ለተገኘው አገልግሎት በትክክለኛው ማስረጃ ሳይደገፍ እንደወጪ ሂሳብ መመዝገቡ እና መከፈሉ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ስለማይቻል ማስረጃው የሚመለከተው የስራ ክፍል ማቅረብ አለበት፡፡

1.14.1 <u>ግኝት፣ያለአግባብ የተከፈለ ውሎ አበል</u>፣

ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በቁጥር ሲ.ሰ.ሚ.30/ጠ13/40/883 ቀን 29/10/04 የመንግስት ሠራተኞች የቀን ውሎ አበል አከፋፈል መመሪያ ላይ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 3 "የውሎ ገባ አበል ማለት አንድ የመንግስት ሠራተኛ ከመደበኛ የሥራ ቦታው ውጭ ወደ ሌላ የሥራ ቦታ ሄዶ ዕለቱን የሚመለስ ከሆነ ለምግብ ለሚያስፈልገው ወጪ የሚከፈል አበል ነው፡፡" ይላል በዚህ መሰረት ስለመተግበሩ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በድምሩ ብር 32,200.00 ከደንብ ውጭ ከተማ ውስጥ ለተደረገ ዝውውር ውሎ አበል ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ **ዝርዝሩን በአባሪ 3 ቀርቧል፡፡**

- በተጨማሪም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በወጪ ማስመስከሪያ 12097 በ16/09/2009 ለ29 ሠራተኞች በተለያዩ ክልሎች የለውጥና የመልካም አስተዳደር ሥራዎች ሱፐርቪዥን ለወጡበት በሚልበድምሩ ብር 266,429.00 የተከፍለ ቢሆንም፣ ከቀረበው ማስረጃ ማረጋገጥ እንደተቻለው መከፈል የነበረበት ብር 95,447.00 ሲሆን፣ በብልጫ ብር 170,982.00 ያለአግባብ ተከፍሎ መገኘቱ ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝሩ በአባሪ 4 ቀርቧል፡፡
- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በቀን 07/05/2010 ዓ.ም ከሰው ሀብት ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት የሠልጣኞች አበልና ትራንስፖርት ወጪ የውሳኔ አስተያየት በቀረበው መሰረት በ23/04/2007 ዓ.ም የቀረበውን ሀሳብ በመጥቀስ በመ/ቤቱ በኩል ለሚሰጡ ስልጠናዎች እና ስብሰባዎች ሙሉ አገልግሎት ማለትም ቁርስ፣ ምሳ፣ እራት እና መኝታ አገልግሎት ተሰጥቶ "ሰልጣኞች እንደ ስልጠናው ቆይታ ጊዜያቸው ግማሽ የቀን ውሎ አበል ክፍያ እንዲከፈል" በማለት በተሰጠው አቅጣጫ በ2009 በጀት ዓመት በናሙና ካየናው ውስጥ ብር 3,233,339.71 ሙሉ አገልግሎት ተሰጥቶ በተጨማሪ ለቆይታ ግዜያቸው የቀኖቹ የግማሽ አበል መከፈሉን ተረጋግጧል፡፡
- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 11398 በቀን 24/06/2009 ልዩ ድጋፍ የሚሹ ክልሎች ማለትም ሱማሌ፣ ጋምቤላ፣ አፋር እና ቤንሺያንጉል ክልል የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሰራተኞች ለድጋፍ ሲሄዱ የሚመለከተው የስራ ክፍል በየወሩ ከሂሳብ ክፍል እየጠየቀ መላክ ሲገባው ቀድሞ ዳይሬክቶሬቱ በዕቅድ ጊዜ በሚዘጋጀው (TOR) መሰረት የክፍሉ ተጠሪ ስለቆይታው ማረጋገጫ ባላቀረበበት የመስክ ስራው፣ የዓመት እቅድን በወር ብዛት መሰረት በመሰክ ስራ መሆናቸው ሳይረጋገጥ አበል እንደሚወራረድ በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል። በዚህ ደረሰኝ ቁጥር የተከፈለው የአንድ ባለሞያ ብር 32,052.15 የውሎ አበል ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልቻልንም።

1.14.2 <u>በኦዲቱ ወቅት የተሰጠ ምላሽ</u>፣

መልስ አልተሰጠም።

1.14.3 <u>ስጋት</u>፣

- ከመመሪያናደንብውጪየውሎአበልክፍያዎችንመፈፀምየመንግስትውስንበጀትአላግባብወጪእንዲሆንመንገድየሚከፍትአሠራርከመሆኑምበተጨማሪመንግስትንለተጨማሪወጪ ሊዳርግ ይችላል።

- ያላግባብ ክፍያ ሊፈፀም፣ ከበጀት በላይ ክፍያ እንዲወጣ እና የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የአበል አከፋፈል ትክክለኛነት አጠራጣሪ ሊያደርገው ይችላል፡፡

1.14.4 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

- የውሎገባ አበል የመንግስት ሠራተኛ ለሥራ ጉዳይ ሄዶ ዕለቱን ከቀኑ 7 ሰዓት ወይም ከምሽቱ 2 ሰዓት በፊት ለመመለስ ሳይቻል ሲቀር ለምሳ ወይም ለእራቱ ወይም ለምሳና እራቱ የሚከፈል አበል ሲሆን በዚህ መሰረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ እየከፈለ ያለው ትክክለኛ የህግ አግባብነት ስለሌለው እየተከፈለ ያለው ውሎ አበል እንዲቆም እና አላግባብ የተከፈለውም ከሰራተኞቹ ብር 32,200.00 ስለመሔዳቸው ማረጋገጫ በማስቀረብ እንዲረጋገጥ አእንዲደረግ፣ እንደዚሁም በመብለጥ የተከፈለውን ብር170,980.00 እና ብር 3,233,339.71 ከላይ በተዘረዘረው መሰረት ተመላሽ እንዲደረግ፡፡ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለራሱ ብቻ የሚያገለግል የውሎ አበል አከፋፈል የውስጥ መመሪያ ማውጣት አግባብነት የለውም፡፡ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ባወጣው ደንብና መመሪያ መሰረት ብቻ መስራት ይኖርበታል፡፡
- ማናቸውም ክፍያ የሚፈጸምባቸው ሂሳቦች ከመከፈሉ በፊት በመንግስት ህግና ደንብ መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡ የመንግሥት ገንዘብ ከጥፋት ለመካላከልና እና አላግባብ ወጪ እንዳይሆን የተቋሙ ሥራ አመራር በጉዳዩ ላይ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡ አሁንም የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ያልቀረቡ መረጃዎች መቅረብ አለባቸው፡፡ ስለዚህ ሰራተኛው የሚሄድበት ቀን ተጠቅሶ ከክፍሉ መቀመጥ አለበት እንጂ በደፈናው ጥቅምት ወር ብሎ ማስቀመጡ የሂሳብ ክፍል የውስጥ ቁጥጥር ስርዓቱ ደካማ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ስለሆነም በትክክል ሥራ ለተሰራበት ጊዜ ብቻ መከፈሉን በተገቢው ሁኔታ በማጣራትና ማረጋገጥ አለበት።

1.14.1 <u>ግኝት፣ያለደንብና መመሪያ ለሽልማት፣ ለዋንጫና ለሰርትፍኬት የተፈጸመ ክፍያ፣</u>

ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞችና ክፍያን በተመለከተ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያው ሪፐብሊክ የሲቪል ሰርቪስ የደመወዝ ሚኒስቴር ደብደቤ ቁጥር ሲሰሚ30/ጠ10/75/390 በቀን 13/8/2003 ዓ.ም የተላለፈ ሰርኩላር እንደሚያመለክተው ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት የደመወዝ ስኬል እና ጥቅማ ጥቅም የሚወሰነው በሚኒስትሮች ም/ቤት እንደሆነ ገልጿል፡፡ በዚሁ መሰረት ስለመፈፀሙ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በ07/02/2009 ዓ.ም በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 10116 ለ115 ሠራተኞች ለእያንዳንዳቸው ብር 2,000.00 በድምሩ 230,000.00 እና ለ61 ሠራተኞች ለእያንዳንዳቸው ብር 3,000.00 በድምሩ ብር 183,000.00 በጠቅላላው ብር 413,000.00 ግንባር ቀደም ፈጻሚዎች ለማበረታቻ በማለት በሽልማት መልክ ተከፍሎ መገኘቱ፣
- በተጨማሪ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በ25/01/2009 በወጪ ማስመስከሪያ 10126 ለዋንጫና ሰርትፍኬት ብር 65,031.50 ተከፍሎ መገኘቱ፣

በአጠቃላይ ብር 478,031.50 የተዘረጋ እና የተፈቀደ ሥርአት ሳይኖር ያለአግባብ ክፍያ መፈፀሙን ተረጋግጧል፡፡

1.14.2 <u>በኦዲቱ ወቅት የተሰጠ ምላሽ</u>፣

በተጠቀሰው ቁጥርና ቀን የተላለፈው ሰርኩላር እንጂ መመሪያ አይደለም፡፡ ሰርኩላሩ በመንግስት መ/ቤቶች በተለይም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ከመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ውጭ በቦርድ የእራሳቸውን መዋቅር፣ ደመወዝ፣ ልዩ እስኬል እና ጥቅማ ጥቅሞችን (የቤት አበል፣ የኃላፊነት አበል፣ የትራንስፖርት አበል) ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ሳያቀርቡና ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ሳያሳውቁ እያስወሰኑ ሥራ ላይ እያዋሉ ችግር በመፈጠሩ ከሕግ ውጪ የሚደረጉ እንዲህ ዓይነቱ ውሳኔዎች እንዲቆሙ የተላለፈ ነው እንጂ ሽልማትንና ማበረታቻ ሥርዓትን የተመለከተ ሰርኩላር አይደለም፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ መንግስት አገሪቱ ከነበረችበት ድህነት እንድትላቀቅና ሕዝቡ የተሻለ ኑሮ እንዲኖር በጥናት የተለያዩ ፖሊሲዎችና የመንግስትን ሠራተኛ የመፈፀም አቅም ለመገንባት እስትራቴጂዎች ቀይሶ በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡ እነዚህ አቅጣጫዎች በበላይ አመራር በቅርብ የፖለቲካ አመራር እየተሠጠበት ይገኛል፡፡ ተለይተው ሥራ ላይ ከዋሉት ማሻሻያዎች ውስጥ አንዱና ዋነኛው የለውጥ መሣሪዎች ናቸው፡፡ እነዚህ መሣሪያዎች በየጊዜው አፈፃፀማቸው በፖለቲካ አመራሩ እየተገመገመ አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎች እየተወሰደ በመተግበር ለውጥ እያመጣ ይገኛል፡፡

ይህን ለውጥ አጠናክሮ በመቀጠል የመንግስትን አቅም ለመገንባት ለፈፃሚዎች በወቅቱ የማበረታቻው ሽልማት እንዲደረግ የተደረገውም በአጠቃላይ አገሪቱ ውስጥ ያለውን አፈፃፀም በመገምገም ግንባር ቀደም የሆኑ ሠራተኛ ለማበረታታት በከፍተኛ አመራር በተደረገው የፖለቲካ ውሳኔ መሰረት መመዘኛ ተዘጋጅቶ ውጤት ላመጡት አመራሮችና ፈፃሚ ሰራተኞች ለማበረታታት እንዲሸለሙ ተደርጓል፡፡ ለዚሁ ስርዓት ለማበጀት በአሁኑ ወቅት የለውጥ መሣሪያዎቹ ከሙከራ ወጥተው መደበኛ አሰራር እንዲሆኑ በበላይ

አመራር ፖለቲካሊ ስለተወሰነ የማበረታቻ ስርዓት መመሪያ ስራ ላይ ለማዋል አዋጅ ተዘጋጅቶ እንዲጸድቅ ለመንግስት ቀርቦ እየተጠበቀ ነው፡፡

1.14.3 <u>ስጋት፣</u>

ከመመሪያና ደንብ ውጪ ክፍያዎችን መፈፀም የመንግስት ውስን በጀት አላግባብ ወጪ እንዲሆን መንገድ የሚከፍት አሠራር ከመሆኑም በተጨማሪ መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ ሊዳርግ ይችላል፡፡

1.14.4 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ማንኛውም ክፉያ ሲከናወን በአዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ለተፈቀደ ነገር ብቻ መከፈል ይኖርበታል፡፡ መመሪያን መሰረት ያላደረገ ክፍያ አግባብነት እንደሌለው ታውቆ ለወደፊት መሰል ስህተት እንዳይከሰት ጥንቃቄ መወሰድ አለበት፡፡ ባለፈውም በጀት ዓመት ተመሳሳይ ሁኔታ ተፈጥሮ ከደንብና መመሪያ ውጭ እንዳይፈጸም በኦዲት የተገለጸ ለመሆኑ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ከደንብና መመሪያ ውጭ የተፈጸመው ክፍያ ተመላሽ እንዲደረግና የፈቀደውም አካል ተጠያቂ እንዲሆን፡፡ ለወደፊቱም በሚመለከተው አካል ፍቃድ ወይም ጉዳዩን የሚመለከት ደንብ ሳይወጣ ተግባራዊ መደረግ አይኖርርትም፡፡

1.15.1 <u>ግኝት፣ባልተፈቀደ በጀት ለድጋፍ (ስፖንሰር) የተከፈለ የቀጥታ ግዥ እና ያለሂሳብ መደቡ ተመዝግቦ የተገኘ፣</u>

የፌዴራል መንግስት መመሪያ 4/2003 ክፍል 2 አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 1 ላይ “የመንግስት መ/ቤቶች በጀት ክፍያ የሚፈፅመው ወይም ወጪ የሚያደርገው የተፈቀደ በጀት ሲኖር ብቻ ነው” ይላል፡፡ እንዲሁም የወጪ ሂሳቦች የሚያዙትና የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ግንቦት 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሰረት በተገቢው የሒሳብ መደብ የሚመዘገቡ መሆኑን ይገልፃል፡፡ በዚህ መመሪያዎች መሰረት ክፍያው ስለመፈፀሙ ኦዲት ሲደረግ ለፋና ብሮድ ካስት ኮርፖሬሽን አክሲዮን ማህበር፣ መሠለ መልቲሚዲያና የህትመት ስራዎች እና ለዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከል ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ጋር እስፖንሰር በማድረግ በድምሩ ብር 3,699,305.25 ያለ ሂሳብ መደቡ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ **ዝርዝሩ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡**

ተ.ቁ	እስፖንሰርየተደረጉድርጅቶች	የደረሰኝ ቁጥር	ቀን	የገንዘብመጠን	የተመዘገበ ውየሒ. መደብ	መመዝገብየነበረበት
1	መሠለመልቲሚዲያናየህትመ	BPV-	12/05	113,562.	2241103	2631101

	ትስራዎች	11072	/09	50		
2	ፋናብሮድካስትኮርፖሬሽንአ ክሲዮንማህበር	BPV-10032	16/01/09	57,500.00	2241103	2631101
		BPV-10547	13/03/09	375,530.41	2241103	2631101
		BPV-12132	29/09/09	375,530.41	2241101	2631101
		BPV-10939	18/04/09	375,530.41	2241103	2631101
		BPV-10019	12/01/09	2,152,800.00	2241103	2631101
3	ዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከል አክሲዮን ማህበር	BPV-12352	16/10/09	248,851.52	6174299	2631101
ጠቅላላ ድምር ብር				3,699,305.25		

1.14.2 <u>በኦዲቱ ወቅት የተሰጠ ምላሽ</u>፣

መልስ አልተሰጠም፡፡

1.14.3 <u>ስጋት</u>፣

የመንግሥት ገንዘብ ያለአግባብ እንዲወጣ ምክንያት ሊሆን እና የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ያወጣው የበጀት ህጉንም ያልተከተለ ከመሆኑም በተጨማሪም የመንግሥት ገንዘብ ለምዝበራ መንገድ ሊከፍት ይችላል፡፡

1.14.4 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>፣

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በጀት ዓመቱ የተፈቀደለትን በዕቅድ ለተያዙ ሥራዎች መሆኑን አውቆና ተገንዝቦ በበጀት የሂሳብ መደብ ላልተካተተ ወጪ ክፍያ መፈጸም አይኖርበትም፡፡ የመንግስት መስሪያ ቤት ድጋፍ(ስፖንሰር) ማድረግ የሚችል ከሆነ በጀቱ በሂሳብ መደብ 2631101 ለድጋፍ (ስፖንሰር) ይታወጅ ነበር፡፡ ነገር ግን የታወጀና የተፈቀደ በጀት ሳይኖር በሌላ የሂሳብ መደብ ወጪ ማድረጋ ስለማይቻል ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለሚያደርጋቸው ግብይቶች የመንግሥት ህግንና መመሪያውን ጠብቆ መስራት አለበት፡፡ ይህንን ወጪም የፈቀደ አካል መጠየቅ አለበት፡፡

1.15.1 ግኝት፣ያለ አግባብ ተከፍሎ የተገኘ የትርፍ ሰዓት ክፍያ፣

የትርፍ ሰዓት ክፍያን አስመልክቶ የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ በመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/1999 አንቀጽ 93 ንዑስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ኤጀንሲው በቁጥር መ30/ጠ13/36/8/3 ሰኔ 29 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈው ደብዳቤ የአፈፃፀም መመሪያ የወጣና መመሪያውም ከሐምሌ 1 ቀን 2001 ዓ.ም. ጀምሮ በስራ ላይ እንዲውል ማድረጉ ይታወሳል፡፡ ይሁን እንጂ ከላይ የተገለጸውን መመሪያ ለጊዜው ተግባራዊ ሳይደረግ እንዲቆይ ኤጀንሲውን በቁጥር መ30/ጠ13/37/82 ጳጉሜ 5 ቀን 2001 ዓ.ም ባስተላለፈው ሠርኩላር መሠረት የትርፍ ስዓት ክፍያ ተግባራዊ እንዳይሆን መመሪያ ተላልፏል፡፡ ነገር ግን ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ከገንዘብ እና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር በቁጥር ገ/ኢ/ል/ሚ/1/54/2/ በቀን 17/09/2002 በተላለፈው መሰረት የትርፍ ሰዓት ክፍያን በአንቀፅ 2 ንዑስ አንቀፅ 2.3 "ትርፍ ሰዓት ክፍያ ማለት፡- መንግስት በህግ ካወጣው መደበኛ የሥራ ሰዓት በላይ ለተከናወነ ሥራ በሰዓት ታስቦ ለሠራተኛ የሚከፈል ገንዘብ ነው፡፡" የሚል ሲሆን ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በህጉ መሰረት ስለመስረሰቱ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በድምሩብር ብር 111,505.61 ያለአግባብ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ **ዝርዝሩ በአባሪ-3 ቀርቧል፡፡**

1.15.2 በኦዲቱ ወቅት የተሰጠ ምላሽ፣

መልስ አልተሰጠም፡፡

1.15.2 ስጋት፣

ክፍያው ትክክለኛነት ላያሳይ እና መከፈል ለሌለበት አገልግሎት ክፍያ ሊፈፀም እንዲሁም የመንግስት ውስን በጀት እንዲባክን መንገድ ሊከፍት ይችላል፡፡

1.15.4 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ለመልካም አስተዳደር ስራዎች አፈፃፀም ሱፐርቪዥን ወጥተው በአበል ከተስተናገዱ በኋላ አዲስ አበባ ውስጥ መጥተው ለሚያጠቃልሉት ስራ እንዲሁም የአደረጃጀት፣ የሥራ ምዘናና ክፍያ ጥናት ዳይሬክቶሬት የክፍሉ ዋና ስራው ሆኖ እያለ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሌላ ተጨማሪ የትርፍ ሰዓት ማሰቡ ትክክል አይደለም፡፡ በመሆኑም ከህግ ውጭ የተከፈለው የትርፍ ሰዓት ክፍያ ከወሰዱት ወይም ከሚመለከታቸው ሰራተኞች

ብር111,505.61 ተመላሽ እንዲደረግና ለወደፊቱ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ስራ አመራር በህግና በደንብ ብቻ መስራት እንዲችል ቁጥጥር እና ክትትል ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

1.16.1 <u>ግኝት፣በመብለጥ የተከፈለ የመኪና ጥገና፣</u>

የፌዴራልመንግስትየተሽከርካሪዎችስምሪትእናአጠቃቀምመመሪያቁጥር 32/2004 ክፍልአራትአንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 6 " የመንግስት መስሪያ ቤት ተሽከርካሪዎች ወቅቱን የጠበቀ የኢንሹራንስ ሽፋን እንዲያገኙ ያደርጋል" ይላል፡፡ ይሁን እንጂ የሚ/ር መ/ቤቱ፡-

- የሰሌዳቁጥር 4-04266 ያለ ኢንሹራንስ ሽፋን በውስጥ ማስታወሻ በ15/11/2008 የንብረት አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት በተፃፈ ደብደቤ ያላግባብበተከሰተአደጋከመንግስትካዝናብር 154,242.07 መኪናውን ለማሰራት ክፍያ የፈጸመ መሆኑን፣
- እንዲሁም የሰሌዳ ቁጥር 4-14032 በ06/04/2007 በቁጥር ምስኢዲ-ኮር/0579/16 ከኢትዮጵያመድንድርጅት ባወጣው ጨረታ አሸናፊው ዝቅተኛ ዋጋ ካቀረበው ድርጅት ጥገናው እንዲሰራ ያቀረበ ቢሆንም ሚኒስትር መስሪያ ቤቱ በ12/06/2007 በቁጥር ስሰሚ/መዴ2/028/07 በሞኤንኮ ጋራዥ እንዲሰራለት እና ልዩነቱን ለመክፈል በገባው ቃልየጥገናውወጪ ጠቅላላ ብር 1,498,573.36 የተጠየቀ በመሆኑ ከኢትዮጵያ መድን ድርጅት ለሚኒስቴሩ በ26/12/2008 በቁጥር ምስአዲ/ኮር/0579/16 በተፃፈ ደብዳቤየመድንድርጅትብር 926,473.72 ድርሻእንደሆነናየቀረውብር 572,099.64 ደግሞ በሚኒስቴርመስሪያቤቱ ልዩነቱን እሸፍናለሁ ባለው መሰረት እንዲሸፍን በማለቱ በብልጫ በወጪማስመስከሪያቁጥር 00009942 በ10/01/2009 ዓ.ምየተከፈለመሆኑን፣

በድምሩ ብር 726,341.71 የኢንሹራንስ ሽፋን እያለ ያለአግባብ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ካዝና በመብለጥ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

1.16.2 <u>በኦዲቱ ወቅት የተሰጠ ምላሽ፣</u>

የሰሌዳ ቁጥር 4-04266 የሆነ ተሽከርካሪ የወጣ ወጪ ያላግባብ በተከሰተው አደጋ ከመንግስት ካዝና መውጣቱ አግባቢ አይደለም ለተባለው ያላግባብ የደረሰ አደጋ የሚል መረጃ የሌለና ተሽከርካሪው እንደማንኛውም ተሽከርካሪ ያጋጠመው ብልሽት መሆኑና በዚያ ምክንያት የተጠገነ እንጂ ሌላ ምንም ዓይነት አደጋ በተሽከርካሪ አካል ላይ የደረሰ ጉዳት የሌለ መሆኑን መረጃዎቹ ያስረዳሉ፡፡ በዚሁ መስረት በወቅቱ የነበሩት አመራሮች ለጥገናው ከካምፒኒ ጋር በተለያየ ጊዜ የተጻጻፉትን ደብዳቤዎች ኮፒ 6 ገጽ አባሪ ተደርጓል፡፡ በቀጣይም እንደተቋም የተሽከሪካሪዎች አያያዝና አጠቃቀምን በተመለከተ ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ላይ የሚገኝ ሲሆን በዚህ ዙሪያ በሚታዩት ክፍተቶች አፋጣኝ የማስተካከያ እርምጃዎችም እየተወሰዱ ይገኛሉ፡፡ በቀጣይም አጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

1.16.3 <u>ስጋት፣</u>

የሚኒስቴር መ/ቤቱ መኪና አደጋ ሲያጋጥም ያለአግባብ ተጨማሪ ክፍያ መክፈል ለሌለበት አገልግሎት ክፍያ ሊፈፀም ይችላል፡፡ እንዲሁም የመንግስት ውስን በጀት እንዲባክን በር ሊከፍት ይችላል፡፡

1.16.4 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመንግስት ንብረት ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መጠቀም እና አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ ያለበት ሲሆን የመኪኖች አደጋ ሲያጋጥም ማስጠገን ያለበት በገባው የእንሹራንስ ሽፋን እንጂ ከመ/ቤቱ ካዝና መክፈል የለበትም፡፡ከስራ ክፍሉ በውስጥ ማስታወሻ ለክቡር ሚኒስቴር የመልካም አስተዳደር ዘርፍ በቀረበው ያላግባብ የደረሰ መሰበር እንደሆነ አመላካች በመሆኑና ኢንሹራንስ በወቅቱ ያለመመልከቱ ስለሚያስረዳ መሰራት ያለበት በገባው የኢንሹራንስ ሽፋን እንጂ ከመ/ቤቱ ካዝና መክፈል አልነበረበትም፡፡ ለወደፊቱ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ስራ አመራር በህግና በደንብ ብቻ መስራት እንዲችል ቁጥጥር እና ክትትል ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

2. የተሰብሳቢ ሂሳብ፣

2.1.1 ግኝት፣በሪፖርቱ እና በዝርዝር ቋቱ የታየው የተሰብሳቢ ሂሳብ ልዩነት፣

የፌደራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 5 በንዑስ አንቀጽ (ለ) "የስራ ማስኬጃ ቅድሚያ ክፍያ በ7 ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት" እና በንዑስ አንቀጽ (መ) "ተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብለት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ" መመሪያው ያመለክታል፡፡ ይሁን እንጂ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሂሳብ መግለጫ ሪፖርት በድምሩ ብር 23,590,414.87 ተሰብሳቢ ሂሳብ የሚታይ ሲሆን፣ የዝርዝር መነሻ ቋት ድምር ግን ብር 28,729,588.034 በመሆኑ ከመነሻ ሂሳብ ወይም ከመወራረጃ ሰነዱ ጋር ሲገናዘብ፣ ልዩነት ያለው መሆኑን ተረጋግጧል፡፡ ለአብነት ያህል ዝርዝሩ ቀጥሎ ቀርቧል፡-

የሂሳብመደብ	ሂሳቡየሚፈለግበትግለሰብ /ድርጅት/ስም	ሰኔ 30/2008 የነበረውብብር ሒሳብሚዛን	ሰኔ 30/2009 ያለውሒሳብሚዛንበብር	ልዩነት	ምክንያት
5217109	መላክተረዲግ	0	30,999.98	30,999.98	ሰነድበማጣራትላይነን
5212601	ከአዲስአበባሲቪልሰርቪስእናየመልካምአስተዳደርቢሮ	1,369,905.22	405,492.81	964,412.41	2006 ዓ.ም -ህዳር 2009 በድጋሚ
5217109	ቤንሻንጉልክልላዊመንግሰት	21,842.79	0	21,842.79	በተደጋጋሚበደብዳቤ ተጠይቋል
5217109	አማራሲቪልሰርቪስና እናየመልካምአስተዳደርቢሮ	5,457,718.12	4,977,015.13	480,702.99	በሰኔወር 2006 ዓ.ም
5217205	አልታኮመፔቴክ	0	155,646.75	155,646.75	በጥቅምትወር 2009 ተሰብስቧል

2.1.2 በኦዲቱ ወቅት የተሰጠ ምላሽ፣

መልስ አልተሰጠም፡፡

2.1.3 ስጋት፣

ተሰብሳቢ ሂሳብ በተቀመጠለት መመሪያ መሰረት ካልተወራረደ የመንግስት ገንዘብ ተይዞ እንዲቆይ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ ሂሳቡ ወደ ማይወራረድበት ደረጃ ሊያደርስ ይችላል፡፡

2.1.4 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ስለዚህ አንደ ተሰብሳቢ የተያዙት ሂሳቦች ያሉበት ደረጃ እና ያለው ልዩነት ተጣርቶ በተጠቃለለው የሒሳብ ሪፖርት ላይ የቀረበው ማስረጃ ሊቀርብ ይገባል፡፡

2.2.1 <u>ግኝት፣ማስረጃ ሳይኖረው ተወራርዶ የተገኘ የተሰብሳቢ ሂሳብ፣</u>

የፌደራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 8 በንዑስ አንቀጽ 4 "ለ" የተሰብሳቢ ሂሳብ አያያዝ "የስራ ማስኬጃ ቅድሚያ ክፍያ በ7 ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበትና በንዑስ አንቀጽ 4 "መ" ደግሞ ተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብበት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ መመሪያው ቢያመለክትም፣ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከ2006 በጀት ዓመት የዞረ ሊወራረድ የሚገባው ሳይወራረድ ድጋሚ አበል ለግለሰቦቹ በመሰጠቱ የሚታየው ተሰብሳቢ ሂሳብ በየዓመቱ እየጨመረ በመሄድ አስቀድሞ የተሰጠው ሳይወራረድ ሌላ ተጨማሪ ስለሚሰጥ ከሒሳብ ቋት (ሌጀር) ጋር ያለው ግንኙነት የተለያየ መሆኑን የተመለከትን ሲሆን የቀድሞ ሚኒስቴር አጃቢዎች የነበሩት አቶ ካሳሁን ግርማ እና አቶ ገመቹ መለታ ወደ አሜሪካን ሲሄዱ የወሰዱትን አበል በወቅቱ ያልተወራረደ መሆኑና የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 10905 በቀን 04/04/2009 ዓ.ም እንደተወራረደ ቢገልጽም ቀሪ ዕዳ ብር 24,864.39 አቶ ገመቹ መለታ እና ብር 25,830.38 አቶ ካሳሁን ግርማ ከ2006 በጀት ዓመት ጀምሮ በጠቅላላ ብር 50,697.77 ያልተወራረደ መሆኑን በሰነድ ተረጋግጧል፡፡

2.2.2 <u>በኦዲቱ ወቅት የተሰጠ ምላሽ፣</u>

መልስ አልተሰጠም፡፡

2.2.3 <u>ስጋት፣</u>

በቅድሚያ ክፍያ ወጪ የተደረገው ሂሳብ በጊዜ ገደቡ ውስጥ አለመወራረድ ለሌላ ስራ ሊውል የሚችለውን የመንግስት ገንዘብ በግለሰቦች ተይዞ እንዲቆይ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ ሂሳቡ ወደ ማይወራረድበት ደረጃ ሊያደርስ ይችላል፡፡

2.2.4 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ከተጠቀሱት ሁኔታዎች መገንዘብ እንደሚቻለው ለተለያዩ ወጪዎች በቅድሚያ ወጪ የተደረጉ ሂሳቦች በወቅቱ አለመወራረድ በተደጋጋሚ የሚሰጥ መሆኑን ከማመልከቱም በተጨማሪ በበጀት ዓመቱ መጨረሻም አጠናቀው ሳያወራርዱ ወደ ሚቀጥለው በጀት ዓመት መተላለፍ፣ ተቋሙ በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር አለማድረጉን

ያመክታል፡፡ በመሆኑምም በተሰብሳቢነት የሚገኘው ሂሳብ በተሰብሳቢ የሂሳብ ቋት ላይ እንዲታይ በማድረግ ከግለሰቦች ተመላሽ እንዲሆን መደረግ አለበት፡፡ የሥራ አመራሩም የመንግሥት ገንዘብ ወጪ ሆኖ እንዳይቀር አፋጣኝ እርምጃ እንዲወስድ፤ ለወደፊቱም ተቋሙ የፋይናንስ ደንብና መመሪያ ተከትሎ መሥራት ይኖርበታል፡፡

3.<u>የተከፋይ ሂሳብ፣</u>

3.1 <u>ግኝት፣</u> <u>ለማን እንደሚከፈል ዝርዝር ሰነድ የሌለው ተከፋይ፣</u>

የፌደራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 5 በንዑስ አንቀጽ (ሀ) "ማናቸውም ክፍያ የሚፈጸምባቸው ሂሳቦች ተከፋይ ሂሳብነታቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሲቀርብና ስልጣን ባለው አካል ሲፈቀድ ብቻ በተከፋይ ሂሳብ መያዝ እንዳለበት" እና በንዑስ አንቀጽ (ሐ) "መ/ቤቶች ከተለያዩ አካላት ቀንሰው ያስቀሩትን የግብርና ሌሎች ሂሳቦች ለሚመለከተው ግብር አስገቢ አካል ወቅቱን ጠብቀው ማስተላለፍ እንዳለባቸው" መመሪያው የሚያዝ ቢሆንም፣ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለአቅራቢዎች ብር 5,662.86፣ ለመንግስት መስሪያ ቤቶች ብር 31,042.56፣ የተለያዩ ክፍያዎች ብር 355,987.62 እና የዋስትና ተከፋይ ብር 1,027,648.48 በጠቅላላው ብር 1,420,341.52 የተከፋይ ሂሳብ በሪፖርት የሚታይ ሲሆን፣ ለማን ለማን እንደሚከፈል ከመቼ ጀምሮ በተከፋይ ሂሳብ እንደሚታይ ሰነድ/ማስረጃ ለማረጋገጥ ተረጋግጧል፡፡

3.2<u>በኦዲቱ ወቅት የተሰጠ ምላሽ፣</u>

መልስ አልተሰጠም፡፡

3.3 <u>ስጋት፣</u>

- ከሰራተኞች ደመወዝ የሚቀነሱ የተለያየ ተቀናናሽ ሂሳቦች ለተጠቃሚዎቹ በወቅቱ ገቢ አለማድረግ (አለመክፈል) ገንዘቡ ከዕቅድ ውጭ ለሆነ ሥራ እንዲውል መንገድ ከመክፈቱም በተጨማሪ ለበጀት ክትትልና ቁጥጥር አመቺ ላይሆን ይችላል፡፡
- የተሰበሰበ ግብር በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ገቢ አለማድረግ ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡

3.4 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ከሰራተኞች ደመወዝ የሚቀነሱ ሂሳቦች ወዲያውኑ ለተጠቃሚዎቹ እንዲከፈሉ፤ በሥራ እንቅስቃሴው የሚሰበስበው ታክስ መንግሥት በዕቅድ ለያዛቸው ልማት ሥራዎች እንዲውል በወቅቱ ለሚመለከተው አካል ገቢ እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት

ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም ተከፋይ ሂሳቦች ለማን ለምን እንደሚከፈል ጠርተው መቀመጥ አለባቸው፡፡ አሁንም ያለበትን ደረጃ ከነማስረጃው ሊቀርብ ይገባል፡፡

4. <u>የበጀት ሂሣብ፣</u>

4.1.1 <u>ግኝት</u>፣ <u>በተቀናጀ የፋይናንስ መረጃ አስተዳደር ሥርዓት /IFMS/ ያልተመዘገበ የመደበኛ በጀት</u>

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የበጀት አስተዳደር፣ አጠባበቅ እና አጠቃቀም በፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል 3 አንቀጽ 02 ንዑስ አንቀጽ 1 "የበጀት ቁጥጥር" "ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደለትን የመደበኛም ሆነ የካፒታል በጀት አጠቃቀም በሚገባ ለመቆጣጠር እንዲችል የበጀት መቆጣጠሪያ መዝገብ ወይም የተዘረጋ የኤሌክትሮኒክስ መረጃ ሥርዓት አመዘጋገብ ሊኖረው ይገባል፡፡" ይላል፡፡ በመመሪያ መሰረት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ መስራቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ከሀምሌ 1 ቀን 2008 እስከ ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ድረስ ያለውን የተጠቃለለውን የሂሳብ መግለጫ የበጀት ምዝገባው ለየፕሮግራሞቹ የታወጀ የተስተካከለው በጀት ከተቀናጀ የፋይናንስ መረጃ አስተዳደር ሥርዓት /IFMS/ ከተመዘገበው ጋር ሲገናዘብ፣ ለፕሮግራም 01 ሥራ አመራርና አስተዳደር ሚኒስቴር ፅ/ቤት-0101 በሒሳብ መደብ 2221103 (ለመስተንግዶ) የተደለደለው ብር 670,000.00 ሲሆን ተጨማሪ በጀት ብር 1,897,782.50 ጠቅላላ ብር 2,567,782.00 መሆን ሲገባው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ብር 2,537,782.20 ብሎ በመመዝገቡ ከተደለደለው በጅት በብር 30,000.00 ልዩነት ያለው መሆኑን ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም መደበኛ በጀት በተቀናጀ የፋይናንስ መረጃ አስተዳደር ሥርዓት /IFMS/ የተመዘገበው በብር 30,000.00 በማነስ የሚታይ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

4.1.2 <u>በኦዲቱ ወቅት የተሰጠ ምላሽ</u>፣

የቀረበው የኦዲት ግኝት ሪፖርት ስህተት ያለው መሆኑን ማመላከት እንወዳለን። ይኸውም በአራቱ ፕሮግራሞች ውስጥ የሥራ አመራር አስተዳደር /ፕሮግራም አንድ/ በሠንጠረዥ በኦዲት የተገኘ ተብሎ የቀረበው ብር 54,748,504.50 ሳይሆን ትክክለኛው 54,718,504.50 ነው። ስለዚህ 30,000 በማነስ በሲስተም ያልተመዘገበ ተብሎ የተገለጸው የኦዲት ግኝት ሪፖርቱ ስህተት እንደሆነ ይታወቅ።

<u>በዝርዝር ሲታይ</u>

ለፕሮግራም አንድ የፀደቀ በጀት 51,592,600.00

ከገንዘብ ሚኒስቴር ተጨማሪ በጀት	3,125,904.50
በበጀት ዝውውር የተሞላ	1,341,695.00
ኦዲት ግኝት ተብሎ መቅረብ ያለበት	54,718,504.50
በኦዲት ግኝት የተያዘ	54,748,504.50
ልዩነት /ስህተት/	30,000ማስታወሻ ለበለጠመረጃ

የፕሮግራም አንድ በጀት አጠቃቀም በዝርዝር አንድ ገጽ ተያይዟል፡፡

4.1.3 ስጋት፣

የታወጀን በጀት በተቀናጀ የፋይናንስ መረጃ አስተዳደር ሥርዓት ውስጥ አለመመዝገቡ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱን የበጀት ቁጥጥር ስርዓቱ ደካማ መሆኑ አመላካች እና ወደ መ/ቤቱ የሚመጡትን የመንግስት ገንዘብ ያላግባ ብ እንዲወጣ በር ከፋች አሰራር መሆኑን አመላካች ሊሆን ይችላል፡፡

4.1.4 የማሻሻያ ሀሳብ፣

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የመደበኛም ሆነ የካፒታል በጀት የታወጀውን ከተዘዋወረና የተስተካከለውን በየፕሮግራም በጀት አስተካክሎ መመዝገብ አለበት፡፡ ለሂሳብ እንቅስቃሴ መነሻው የበጀት ክፍል እንደመሆኑ የበጀት ክፍሉ ደካማ መሆን የሂሳብ እንቅስቃሴውን በሙሉ ደካማ ስለሚያደርገው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከዚህ በፊት የነበረውን የበጀት ቁጥጥር ስርዓቱን ይዞ መሄድ ይገባዋል፡፡

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በማነስ አይታይም ቢልም የመደበኛ በጀት የሥራ አመራርና አስተዳደር ሚኒስቴር ፅ/ቤት- ፕሮግራም 0101 ብር 30,000 ልዩነት መኖሩ ትክክል ስለሆነ የበጅት ክፍሉ የመለሰው መልስ ትክክል አይደለም፡፡ የሥራ አመራሩም በበጀት ክፍል ላይ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

4.2.1 ግኝት፣ ባልታወጀ በጀት እንደ ወጪ ተይዞ የተገኘ፣እንዲሁም ከተፈቀደ ወይም ከተዛወረወ በጀት በላይ ተጠቅሞው የተገኘ ፣

የፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል 1 አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 9 "የበጀት ቁጥጥር፡- ማለት በተፈቀደው የበጀት ዝውውር ላይ በማዕከላዊነት ቁጥጥር ለማድረግ እንዲቻል ተገቢውን መረጃ ለማግኘት ወይም ውሳኔ ለመሰጠት እንዲሁም ከበጀት በላይ ወጪ ያለመደረጉን ለመቆጣጠር የሚረዳ የበጀት አመዘጋገብ ስርዓት ነው፡፡" ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዚሁ መሰረት መስራቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡

- የ2009 የታወጀ በጀት ሳይኖር ከመደበኛ በጀት ብር 3,554,091.09 እና ከካፒታል በጀት ብር 1,344,497.50 በሌለ በጀት እንደ ወጪ ተይዞ ተገኝቷል፡፡ በድምሩ ብር 4,898,588.59 ባልታወጀ በጀት እንደ ወጪ ተይዞ መገኘቱን ተረጋግጧል፡፡
- ከተፈቀደ ወይም ከተዘዋወረው በጀት በላይ ከመደበኛ ብር 10,119,113.04 እና ከካፒታል በጀት ብር 8,969,702.97 ከበጀት በላይ እንደ ወጪ ተይዞ ተገኝቷል፡፡ በድምሩ ብር 19,088,816.01 ከተፈቀደ በጀት በላይ መጠቀሙን ተረጋግጧል፡፡

4.2.2<u>በኦዲቱ ወቅት የተሰጠ ምላሽ</u>፣

1ኛ የታወጀ በጀት ሳይኖር አንድ ወጪ የተያዘ ተብሎ ለቀረበው፡-

- ✓ የበጀት እጥረት በማጋጠሙ በበጀት ዝውውር የወጣ ወጪ መሆኑ
- ✓ በፕሮግራም 1- 2.5 ሚሊዮን የታወጀ በጀት መሆኑ /የሂሳብ መደብ 2231107/
- ✓ ፕሮግራም 3- 1.7 ሚሊዮን የታወጀ በጀት ወጪ መሆኑ /ኮድ 2311101/ እንዲሁም በዚህ ፕሮግራም በሂሳብ መደብ 2311102 የተያዘም ሆነ የወጣ ወጪ አለመኖሩ
- ✓ በJEG ፕሮጀክት ከታወጀ በጀት የወጣ ወጪና የወጣውም 300.000 ሳይሆን 121400 መሆኑ

2ኛ ከበጀት በላይ ወጪን በተመለከተ

- ✓ በኦዲት ግኝቱ ወጪ ተብለው የቀረቡት ትክክል ሲሆን ወጪው በበጀት ዝውውር የተሸፈነ መሆኑ ይታወቅ
- ✓ የJEG ፕሮጀክትከበጀትበላይወጪተብሎየቀረበውየኦዲትስህተትመሆኑማለትምየፀደቀውንበጀትበወጪበአዲስመያዙየተፈጠረስህተትመሆኑ፣

4.2.3 <u>ስጋት፣</u>

ከበጀት በላይ ወጪ ማውጣት መንግስት ላላስፈልጊ ብድር ሊዳረግ እንዲሁም ተጠያቂነትን ሊያስከትል እና የመንግስት ገንዘብ ያላግባብ ላልታቀደ እና በዕቅድ ላልተያዙ የወጪ አርዕስት ሊወጡ እና ሊሰሩ የታቀዱት ስራዎች ደግሞ ላይሰሩ ይችላሉ፡፡

4.2.4 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተፈቀደ በጀት መኖሩን ሳይረጋገጥ ከተፈቀደለት በጀት በላይ ወጪ ማድረግ ተጠያቂነትን እንደሚያስከትል እና መ/ቤቱ የተፈቀደለትን በጀት በመንግስት የፋይናንስና በጀት አዋጅ መሠረት መጠቀም ይኖርበታል፡፡አሁንም ከበጀት በላይም ወይም ያልተፈቀደ በጀት

መጠቀም አግባብነት የለውም። የበጀት ዝውውርም የሚፈቀደው በአንድ ንዑስ አርዕስት ወይም ንዑስ ንዑስ አርዕስት ውስጥ በዋና የሂሳብ መደብ ስር ባሉ የወጪ መደቦች ውስጥ ብቻ ማዛወር ይቻላል፡፡ ከዚያ ውጭ ያሉትን ግን ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በራሱ ማዛወር እንደማይችላ መመሪያው የሚያመለክት ስለሆነ በስራ ክፍሉ በኩል የተሰጠው መልስ አጥጋቢ አይደለም፡፡ ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ እንዳይሆን የተቋሙ ሥራ አመራር በበጀት አጠቃቀም ላይ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል።

4.3.1 <u>ግኝት</u>፣ <u>ሥራ ላይ ያልዋለ የመደበኛ እና የካፒታል በጀት፣</u>

የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የበጀት አስተዳደር፣ አጠባበቅ እና አጠቃቀም በፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 እና በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 ክፍል 3 አንቀጽ 12 መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ2009 በጀት ዓመት ለየፕሮግራሞቹ የተመደበው የወጪ በጀት እና ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር፣ ከመደበኛ በጀት ብር 28,446,992.95 እና ከካፒታል በጀት ብር 44,426,074.32፣ በድምሩ ብር 72,873,067.27 ያልተሰራበት በጀት ተገኝቷል፡፡

4.3.2 <u>በኦዲቱ ወቅት የተሰጠ ምላሽ፣</u>

የመ/ቤቱን በጀት አስተዳደር በበላይነት የሚመራው እቅድና በጀት ቁጥጥርና ክትትል መሆኑ ጥያቄው ለእነሱ ቢቀርብላቸዉ ጥሩ ነው፡፡

በዕቅድና በጀት ዳይሬክቶሬት የበጀት አጠቃቀም ማነስ ምክንያት

1ኛ. የስራ ክፍሎች በጀታቸውን ተከታትለው በአግባቡ ጥቅም ላይ አለማዋል

2ኛ. የበጀት አስተቃቀደ ክህሎት ችግር

3ኛ. ግዥ በወቅቱ አለመፈፀምን የፋይናንስ ክፍል የአቅም ችግር ሲሆን

4ኛ. በሌላ በኩል የቀርበው የበጀት አጠቃቅም ከፀደቀው በጀት መሆኑና የተዛወረውን በጀት በወጪ አለመያዙ አፈፃፀሙን ዝቅ እንዲል አደርጎታል ለበለጠ መረጃ የሁሉንም ፕሮግራሞእ 6 ገፅ ተያይዟል፡፡

4.4.3 <u>ስጋት፣</u>

በበጀት ዓመቱ ተራፊ በጀት መገኘት በሌሎች መ/ቤቶች ሊሠራበት የሚችለውን በጀት የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ስም ተይዞ እንዲቆይ ያደርጋል፡፡

4.3.4 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

በየወሩ በሥራ ክፍሉ በሚቀርበው የበጀት አጠቃቀም ሪፖርት መሠረት ተራፊውን በጀት በመ/ቤቱ ስም ተይዞ እንዳይቆይ በሌሎች መ/ቤቶች እንዲሰራበት ሪፖርት እንዲደረግ፣ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ተቋሙ የተፈቀደለትን በጀት በመንግስት የፋይናንስና በጀት አዋጅ መሠረት መጠቀም ይኖርበታል፡፡

5. <u>ንብረት፣</u>

5.1.1 <u>ግኝት</u>፣ <u>የመረጃ አያያዝ ንብረቶች ርክክብ በተመለከተ፣</u>

የኢትዮጵያ ፌዴራል መንግስት የፋይናናስ አስተዳደር ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ቁጥር 648/2001 ክፍል 10 አንቀጽ 58 የንብረት ጥበቃ፣ ቁጥጥር እና ማስወገድ ንዑስ አንቀጽ 1 “የመንግስት ንብረት በሚገባ የተመዘገበና የክትትል ስርዓት የተዘረጋለት” መሆን እንዳለበት አዋጁ ያዛል በዚህ መሰረት ስለመሰራቱ ኦዲት ሲደረግ በ1800 ከትረጀሪ ለተቀናጀ የሲቪል ሰርቪስ መረጃ አያያዝ ስርዓት ፕሮጀክት /ICMIS/ ለየክልሎቹ የሚሰጡ ንብረቶች በህጉ መሰረት ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በናሙና ካየናቸው ውስጥ ዴስክ ቶፕ ኮምፒዉተር ኮር አይ 3 ብዛት 400ና ዩፒኤስ ብዛት 350 ዋጋቸው ብር 7,150,872.5 ለኦሮምያ፣ ለአማራ፣ ለደቡብ፣ ለትግራይና ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሲሰራጭ በትክክል ስለመድረሱ ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

አቅራቢ ድርጅት ስም	ቀን	የወጪ ማስመ ስከሪያ	የዕቃው አይነት	የገንዘብ መጠን
አልታ ኮምፒዩቴክ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር	24/08/09	11911	አልታ ኮምፒዩቴክ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር	4,653,360.00
ኤ.ኤስ.አትሬዴ ንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር	13/08/09	11902	ዩፒሶች	2,497,512.50
			ጠቅላላ ድምር ብር	7,150,872.50

5.1.2<u>በኦዲቱ ወቅት የተሰጠ ምላሽ፣</u>

የተባሉት ንብረቶች ስለመድረሳቸው ክልሎች ማስረጃ ኮፒ አድርገው ልከዋል፡፡ ለፌደራል ዋና ኦዲተር ባለሞያዎች ቀርቧል፡፡ አሁንም በድጋሚ እንዲቀርብ ከሆነ አያይዘን ልክናል፡፡

5.1.3 <u>ስጋት፣</u>

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር ያወጣን የቁጥጥር ስርዓት ተከትሉ ካልሰራ ንብረቱ ላልታለመለት አላማ ሊውል እና የመንግስት ሀብት ያላግባብ ሊጠፋ ይችላል፡፡

5.1.4 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ማንኛውንም ንብረት ለክልሎች ሲያሰራጭ ስለመድረሱ ክልሉ ሞዴል 19 ዋናው (ኦርጅናል) ገቢ ደረሰኝ ቆርጦ ሲያመጣ ንብረት ስለመድረሱ ማረጋገጫ ስለሚሆን መያዝ አለበት፡፡ በኮፒ ሰነድ ስለማይወራረድ ንብረቱ ለታለመለት አላማ ስለመዋሉ ማረጋገጥ አይቻልም፡፡ ስለዚህ አሁንም ክልሎች ከደረሰ ስለመድረሱ ማረጋገጫ ዋናውን ማስረጃ መላክ አለባቸው፡፡ ለወደፊቱም የስራ አመራሩ ጥንቃቄ ማረግ አለበት፡፡

5.2.1 <u>ግኝት፣በንብረት ወጪ ደረሰኝ ወጪ ሆኖ የተገኘ፣</u>

የፌደራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ክፍል 3 አንቀጽ 13 (ቸ) "የስቶክ ወጪ መጠየቂያ ተጠቃሚ የሥራ ክፍሎች ወይም ሠራተኞች ለስራ የሚያስፈልጋቸውን ንብረት በሚፈልጉበት ወቅት የዕቃ መጠየቂያ ቅጽ በተገቢው ሁኔታ በመሙላትና በሚመለከተው ኃላፊ በማስፈረም የንብረት ክፍል አስተዳደር ተግባርን ለሚያከናውን የሥራ ክፍል ማቅረብ ይኖርበታል፡፡" የሚል ሲሆን የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ንብረት ክፍል ኦዲት ሲደርግ፣ በዓመቱ መጨረሻ በቆጠራ ፈሰስ እንዳይሆን በግራውንድ (B2) 27 ጎማ፣19 ካለማደሪያ እና 15 ፍላፕ የተገኙና ንብረቶቹ ለምን እንደተቀመጠ የንብረት አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክተር ሲጠየቁ በትራንስፖርትና ሥምሪት አገልግሎት ኃላፊ በኩል የወጣ እና ከበላይ አመራር በተሠጠው አቅጣጫ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ የዕቃ ወይም የንብረት ወጪ ደረሰኝ ሞዴል 22 ቁጥር 078361 በ30/2009ዓ.ም የብር 66,172.11 ከንብረት ክፍል ወጪ ሆኖ ለብቻው የተቀመጠ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡ ዝርዝሩ ቀጥሎ ቀርቧል፡-

ተ.ቁ	የዕቃውአይነት	ብዛት	ያንዱዋጋ	ጠቅላላዋጋ
1	አዲስጎማ 750–16 10PR PC	15	2,494.40	37,415.93
2	አዲስጎማ 700–15 10PR PC	10	2,101.48	21,014.75
3	ከመንዳሪ 750–16 0PR	9	212.44	1,911.96
4	ከመንዳሪ 700–15 0PR	10	173.21	1,732.13
5	ማታዶርጎማ 175/70R	2	1,051.80	2,103.60
6	ፍሊፕ	15	132.92	1,993.76
			በጠቅላላ ድምር ብር	<u>66,172.11</u>

5.2.2<u>በኦዲቱ ወቅት የተሰጠ ምላሽ፣</u>

ከተራ ቁጥር 1-5 የተዘረዘሩት ንብረቶች ግዥ የተፈጸመው በሰኔ ወር መጨረሻ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የገባ በመሆኑና ጐማዎቹን የሚጠቀመው ተሽከርካሪዎች በወቅቱ ልዩ ድጋፍ የሚሹ ክልሎች መስክ ሥራ ተሰማርተው ያልተመለሱ በመሆኑ ምክንያት በመሆኑ፣ እንደተቋም ያለን ስቶር ውስንና ወደ ሌላ ስቶር ማለትም B2 እንዲቀመጥ የተደረገ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ ንብረቱን ለማሸሸ ፊሰስ እንዳይደረግ ተፈልጐ አለመሆኑ እንዲታወቅልን እያልን በአሁኑ ሰዓት ጐማዎቹ ለተጠቃሚዎች የተሰራጨና አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡ ነገር ግን የበላይ አመራሩ አለ የተባለው ትክክል አይደለም፡፡ በአጠቃላይ ንብረቶቹ በማዕቀፍ የሚገዛ በመሆናቸው ምክንያት እና በተጠየቀ ጊዜ ተገዝቶ ባለመምጣቱ፣ እንዲሁም ተሽከርካሪዎቹም በመስክ ሥራ ላይ በመሆናቸው እና የዕቃ ማስቀመጫ ቦታ ጥበት በመኖሩ ምክንያት ነው፡፡

5.2.3 ስጋት፣

የሚጠቀምበት ሹፌር ባልጠየቀበት ሆኔታ በበላይ አመራር ትዕዛዝ ንብረቱ ወጥቶ በሌላ ቦታ መቀመጡ የመንግስት ንብረት ያላግባብ እየባከነ መሆኑን አመላካች ሊሆን እና ውስን የመንግስት ገንዘብ ያላግባብ እንዲባክን ሊያደርግ ይችላል፡፡

5.2.4 የማሻሻያሀሳብ፣

የግዥና ንብረት ጠቅላላ አገልግሎት ዳሬክቶሬት ሀጉ ከሚለው ውጭ በላይ አመራር ስለታዘዝኩ በትራንስፖርትና ሥምሪት አገልግሎት ኃላፊ በኩል ወጪ እንዲሆን አድርገናል ማለቱ ትክክለኛ አሰራር ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የትራንስፖርትና ሥምሪት አገልግሎት ኃላፊ ሹፌሮች ባልጠየቅበት ብር 66,172.11 የሚያወጣ ንብረት በስሙ ማውጣቱ ትክክል ስላልሆነ ለወደፊቱ በህጉ መሰረት ብቻ መስራት ይጠበቅበታል፡፡ የስራ አመራሩም እንደዚህ ያለ ትዕዛዝ መስጠት መመሪያን መጣስ ስለሆነ መታረም አለበት፡፡ ከግምጃ ቤት ወጪ ተደርጎ ለተጠቃሚ በሚሰጥበት የዕቃ ማስረከቢያ ሞዴል አማካኝነት ወጥቶ ለተጠቃሚው ብቻ መሰጠት ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱ ይህን አይነት አሰራር መሰራት የለበትም፡፡

5.3.1 ግኝት፣የተሽከርካሪ እና ነዳጅ አጠቃቀም፣

የፌዴራልመንግስትየተሽከርካሪዎችስምሪትእናአጠቃቀምመመሪያቁጥር 32/2004 ክፍልአራትአንቀጽ 9 ንዑስየመንግስትተሽከርካሪዎችነዳጅ፣ቅባት፣ዘይትአጠቃቀምእናቁጥጥርአንቀጽ 2 "ለበላይኃላፊዎችእናለኃላፊዎችከሚመደቡተሽከርካሪዎችበስተቀርእያንዳንዱተሽከርካሪየ ፈጀውየነዳጅመጠንከሽፈነውየኪ/ሜትርመጠንጋርእየተመዘገበተገቢውሪፖርትበየወሩመቅ ረብእንደሚኖርበት" በተጨማሪም የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 አንቀጽ 6 የቋሚ ንብረት አመዘጋገብ በሚለው ስር ‹‹የመንግስት ንብረት ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መጠቀም እና አገልግሎት እንዲሰጥ የጥገና ስርዓት መዘርጋት እንዳለባቸው›› በማለት መመሪያው ቢያመለክትም፣ ሚኒስቴርመስሪያቤቱበዚሁመሰረትስለመስራቱለማረጋገጥኦዲትስናደርግ፡-

- በ2009 ዓ.ምከወጣውነድጅናቅባቶችበሒሳብመደብ 6217 ብር 2,760,000.00 ለፑልአገልግሎትየሚውሉመኪኖችስንመለከትየተጠቀሙበትንየነዳጅመጠንናከሸፈ ኑትየኪ/ሜትርበየጊዜምዝገባእየተከናወነቢሆንምየማቀናነስ (የማስታረቅ) ስራበጌጅበማንበብበርቀትእንደማይሰራተረጋግጧል፡፡ የነዳጅፍጆታየሚሞላውበሔዱበትኪ.ሜትርሳይሆንበሚሄዱበትስፍራበግምትየሚሰላ መሆኑን፣
- የመስሪያቤቱሰራተኛምሆነሀላፊከመስሪያቤቱሲለቅንብረትማስረከብእንዳለብየመን ግስትመመሪያቢያመለክትምየቀድሞክብርትሚኒስቴርወ/ሮአስቴርማሞይገለገሉበ ትየነበረመኪናየሰሌዳቁጥር 4-18419 ቶዮታያሪስእና 4-14234 V8 ቶዮታእንዲሁምክቡርሚኒስቴርዴኤታአቶተመስገንጥላሁንየሰሌዳቁጥር 4-17243 ቶዮታያሪስእና 4-15370 V8 ቶዮታመኪኖችያላስረከቡመሆኑን፡-

5.3.2በኦዲቱ ወቅት የተሰጠ ምላሽ፣

ለፑል አገልግሎት የሚውሉ ተሽከርካሪዎች የሚደረግ የነዳጅ እደላ ከዚህ በፊት የተሽከካሪዎች የኪሎ ሜትር ሊኬት/ኖርማላይዘሽን ያልተሰራላቸው በመሆኑ ምክንያት የሚደረግ የነዳጅ እደላ በግምት ነበር፡፡ ይሁን እንጂ የነዳጅ ስርጭት/እደላ በቂ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር እየተደረገ ቢሆንም አልፎ አልፎ መቆራረጥ ያለው

መሆኑን በተደረገው የውስጥ ኦዲት ግኝት ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም እነዚህን ክፍተቶች ለማስተካከል የተለያዩየ እርምት እርምጃዎችን የመውሰድ ስራዎችን ተሰርቷል ፡፡ በዚሁ መሰረት በ2009 ዓ.ም. መጨረሻ ጀምሮ የ25 ተሽከርካሪዎችን የኪሎ ሜትር ሊኬት/ኖርማላየዘሽን በማሰራት ከ2010 በጀት ዓመት ጀምሮ በሊትር ምን ያህል ኪሎ ሜትር እደሚጓዙ በየግዘው የተሽከርካሪው ጌጅ እየተመዘገበ ነዳጅ እየተሰጠ በየጊዜው ለሚመለከተው አካል ሪፖርት እየተደረገ ይገኛል፡፡ የሌሎች የቀሪዎችን ተሽከርካሪዎች ኪሎ ሜትር ሊኬት /ኖርማላይዘሽን ስራን በማጠናነቀቅ ወጥ የሆነ የነዳጅ ስርጭት እንዲኖር ለማድረግ ከአዲስ አበባ ከተማ ምርታማነት ማሻሻያ ማዕከል ሊኬት ለማስደረግ በዝግጅት ላይ ነው፡፡

ለክቡር ሚኒስትሩ ሹፌር ለአቶ ካሳሁን ገመቹ እና አንድ ቶዮታ ፕራዶ ኮድ 4-17551 አቶ ግርማ ዘሪሁን ተረክበው ለፑል ስራና ለአጃቢዎች ጥ.ትና ማታ የሰርቪስ አገልግሎት እየሰጠ ያለ እንጂ አራት ተሽከርካሪዎች ለክቡር ሚኒስትሩ ተሰቷል ተብሎ የቀረበው መረጃ ስህተትና አግባቢነት የሌለው ነው፡፡ ስለዚህ ግለሰቦቹ ተሽከርካሪዎቹን የተረካከቡበትን የመረካከቢያ ፎርም 2 ገጽ አባሪ ተደርጓል፡፡

ክብሪት ወ/ሮ አስቴር ማሞ በስራ ምክንያት ወደ መለስ ዜናዊ አመራር አካዳሚ ተመድበው ሲሄዱ ይዘውት የሄዱትን ተሽከርካሪዎች ለተቋሙ እንድመለሱ ለአካዳሚው በ11/11/2009 ዓ.ም በቁጥር ፕሰሚ/ሚጽ11/143/09 ደብዳቤ የተጻፈ ሲሆን በክትትል ላይ እያለ ገንዘብና ኢኮነኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሁለት ትርፍ መኪናዎችን (አንድ ቪ8 እና አንድ ፕራዶ) ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር እንድንመልስ በ4/01/2010 ዓ.ም. በቁጥር በተ8/6/16 ለተቋማችን በጻፈው ደብዳቤ መሰረት ቪ8ቱን በዚያው ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር እንዲያስረክቡና የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴርም ተሽከርካሪውን እንዲረከቡ በ07/02/2010 ዓ.ም በቁጥር ፕሰሚ/ሚጽ6/21/2010 የተፃፈው ደብዳቤ ለአካዳሚው በግልባጭ የደረሰው ሲሆን ቶዮታ ያሪስ በአሁን ጊዜ ለሚኒስቴር መ/ቤታችን እንዲመለስ ተደርጓል፡፡ የደብዳቤዎች ኮፒ 3 ገጽ አባሪ ተደርጓል፡፡

የክቡር አቶ ተመስገን ጥላሁንን በተመለከተም ክቡር ሚኒስቴር ዴኤታ የሆኑት አቶ ነጋ በርሄ ወደ ተቋማችን ተሹመው ሲመጡ ይዘውት ከመጡ አንድ ቪ8 እና አንድ ቶዮታ ያሪስ ጋር በቅይይር የተላለፈ መሆኑ ነው፡፡

የሰሌዳ ቁጥር 4-04266 የሆነ ተሽከርካሪ የወጣ ወጪ ያላግባብ በተከሰተው አደጋ ከመንግስት ካዝና መውጣቱ አግባቢ አይደለም ለተባለው ያላግባብ የደረሰ አደጋ የሚል መረጃ የሌለና ተሽከርካሪው እንደ ማንኛውም ተሽከርካሪ ያጋጠመው ብልሽት መሆኑና በዚያ ምክንያት የተጠገነ እንጂ ሌላ ምንም ዓይነት አደጋ በተሽከርካሪ አካል ላይ የደረሰ ጉዳት የሌለ መሆኑን መረጃዎቹ ያስረዳሉ፡፡ በዚሁ መሰረት በወቅቱ የነበሩት አመራሮች ለጥገናው ከካምፒኒ ጋር በተለያየ ጊዜ የተጻጻፉትን ደብዳቤዎች ኮፒ 6 ገጽ አባሪ ተደርጓል፡፡ በቀጣይም እንደ ተቋም የተሽከሪካሪዎች አያያዝና አጠቃቀምን በተመለከተ ጥብቅ ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ ላይ የሚገኝ ሲሆን በዚህ ዙሪያ በሚታዩት ክፍተቶች አፋጣኝ የማስተካከያ እርምጃዎችም እየተወሰዱ ይገኛሉ፡፡ በቀጣይም አጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

ስለ አቶ ሀብታሙ አንዳርጌን ጉዳይ በተመለከተ በተቋሙ የሰው ሃብት ልማት አሰተዳደር ዳይሬክቶሬት በኩል ምላሽ የሚሰጥበት እንጂ ስራ ክፍላችን በሠራተኛው ዝውውርም ሆነ ትውስት ዙሪያ ምንም አይነት መረጃ የለውም፡፡

5.3.3 <u>ስጋት፣</u>

- መኪኖች በከተማ ውስጥ እና ከከተማ ውጪ የሚሄዱበትን በኪ.ሜትር ካልተቀመጠ በበጀት ዓመቱ ውስጥ የወጣውን የነዳጅ እና ተዛማጅ ወጪዎች ታማኝነት ሊያሳጣው በህግ ሳይሆን በግለሰቦች አመለካከት ላይ ያተኮረ ሊሆን ይችላል፡፡
- የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱን ንብረት ላልተለመለት አላማ ሊውልና ንብረት በቂ ጥበቃ ላያገኝና ለብልሹ አሰራር መንገድ ሊከፍትና የውስጥ ቁጥጥር ስርዓቱ ደካማ መሆኑ አመላካች ሊሆን ይችላል፡፡
- የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ንብረት ሲበላሽ ወዲያውኑ ጥገና ተደርጎለት አገልግሎት እንዲሰጥ አለማድረግ ለበለጠ ብልሽት የሚዳርግ ከመሆኑም በተጨማሪ መንግስትን አላግባብ ላልሆነ ወጪ የሚዳርግና በመስሪያ ቤቱ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡

5.3.4 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ መንግስት ባወጣው የተሽከርካሪዎች ስምሪት እና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 በሚያዘው መሰረት ብቻ ጌጅ የተሟላና በትክክል የሚሰራ መሆኑን በየጊዜዉ በመከታተል የሸፈነው ኪ/ሜትር ከሚጓዘው መጠን ጋር የማቀናነስ (የማስታረቅ) ስር በመስራት ልዩነቱ መሰላት አለበት፡፡ በህግ ሳይሆን በሔደበት ቦታ ስፍራ

የሚለካ ከሆነ የግለሰቦች አመለካከት ላይ ያተኮረ ይሆናል፡፡ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በመመሪያው መሰረት ብቻ መስራት አለበት፡፡

- በህጉ መሰረት ለሹፌር መኪና ይሰጥ የሚል መመሪያ የሌለ ስለሆነ ለአቶ ካሳሁን ገመቹ እና ለአቶ ግርማ ዘሪሁን የተሰጠ ከሆነ ከመመሪያው ውጭ የተሰጠው ተሽከርካሪ ወደ መስሪያ ቤቱ ተመላሽ እንዲደረግ እንላለን መስሪያ ቤቱ በተቀመጠው መመሪያ ብቻ መስራት አለበት፡፡
- የቀድሞ ሚኒስቴሮች ሲዘዋወሩ ማንኛውንም ሰራተኛ ንብረት እንደሚያስረክበው የነሱንም መረከብ ነበረበት፡፡ ካልሆነ ግን ወደ ተዛወሩበት መስሪያ ቤት ከገ/ኢ/ል ሚኒስቴር በቀን 20/04/08 በቁጥር በተ4/6/7 በተላለፈው መመሪያ መሰረት በቅይይር ማስተላለፍ፤ ወይ ወደ መስሪያ ቤቱ መመለስ ሲገባ ነዳጅ ከመስሪያ ቤቱ መቅዳቱ አግባብ የለውም፡፡ አሁንም የተጀመረው ስራ አበረታች ስለሆነ ቶዮታ ያሪስ ወደ መስሪያ ቤቱ መመለሱን መረጃ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

5.4.1 <u>ግኝት፣የነዳጅ፣ ቅባትና ዘይት አጠቃቀም፣</u>

የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 አንቀጽ 6 የቋሚ ንብረት አመዘጋገብ በሚለው ስር ‹‹የመንግስት ንብረት ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ አገልግሎት እንዲሰጥ የጥገና ስርዓት መዘርጋት እንዳለባቸው›› መመሪያው ቢያመለክትም፤ የፌደራል መንግስት ተሽከርካሪዎች ስምሪት እና አጠቃቀም መመሪያ 32/2004 ክፍል 3 አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 3 “የመስሪያ ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ለመ/ቤቱ ተሽከርካሪዎች የሚውለው ነዳጅ፤ ቅባትና ዘይት የመሳሰሉት ከውጤት ጋር በተገናዘበ መልኩ ስለሚስራጩበት መንገድ ተጨማሪ የውስጥ አሠራርና የቁጥጥር ሥረዓት ይዘረጋሉ፡፡ በየወሩም ሪፖርት እንዲቀርብ ማድረግ ተገቢውን የአፈፃፀም ግምገማ ያካሂዳሉ፡፡” በሚለው መሰረት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ስለመስራቱ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ ለኃላፊ ከተመደበ የነዳጅ መጠን በላይ በመታደሉ ብር 47,065.28 ከተፈቀደ መጠን በላይ የተቀዳ ሲሆን፣ በተጨማሪም ብር 20,228.60 ለስራ ደብረዘይት እና ናዝሬት ሲሄዱ የተቀዳ በጠቅላላ ብር 67,228.60 ከተፈቀደ ውጭ መጠቀሙን እና የቀድሞ ሚኒስቴር የነበሩት ከመስሪያ ቤቱ ከለቀቁ በኃላ በ09/09/09 የጀኔሬተር ነዳጅ እየተሞላ ያለ መሆኑን የሠሌዳ ቁጥር 4-20179 በቀን 14/09/09 100 ሊትር ነዳጅ መሞላቱን ተረጋግጧል፡፡**ዝርዝሩ በአባሪ-6 ቀርቧል፡፡**

5.4.2 በኦዲቱ ወቅት የተሰጠ ምላሽ፣

መንግስት የተሽከርካሪና ነዳጅ አደላን በሚመለከት ለመንግስት የስራ ሀላፊዎች የተፈቀደው ሊትር ከቤታቸው ስራ ቦታ የሚያመላልስ ለከተማ ውስጥ ብቻ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ይሁን እንጂ እነዚህ ኃላፊዎች ለመንግስት ስራ ምክንያት ከከተማ ውጪ ወደ ተለያዩ ክልሎችና ከተሞች ሲሄዱ ተሽከርካሪው በሊትር የሚሸፍነው ኪሎ ሜትር መሰረት እየተሰላ የሚሰጥ እንጂ ከከተማ ውጪ ስለሄደ ብቻ ነዳጅ አይሰጥም፡፡ ከከተማ ውስጥም ቢሆን በመመሪያው መሰረት የተፈቀደላቸውን ኮታ እየተጠቀሙ ይገኛል፡፡

በክብረት ወ/ሮ አስቴር ማሞ እና በክቡር ሚኒስቴር በአቶ ታገሰ ጫፎ ተጨማሪ ነዳጅ ተወስዷል ተብሎ የተገለጸው ትክክል እንዳልሆነና በእነዚህ ኃላፊዎች ስምና ፊርማ የተጠየቀም ይሁን የተወሰደ ነዳጅ የለም፡፡ በእነዚህ ኃላፊዎች ስምና ፊርማ ነዳጅ ስለመወሰዱ የሚገልፅ ሰነድም ሆነ መረጃ የለም፡፡

የሌሎች ሚኒስቴር ዴኤታዎች የነዳጅ ጭማሪዎች ቢሆን እንደ ተቋም የሚሰሩ የተለያዩ ስራዎችን ከከተማ ውጪ የመንግስት ስራ ለመስራት ለመስክ ስራ የሚሰጣቸው ነው፡፡ የቢሮ ኃላፊዎችና መካከለኛ አመራሮችም በተመሳሳይ ለስራ የተሰጣቸው መኪና በራሳቸው እንዲጠቀሙና ሹፌር ተመድቦላቸው ሌላ አላስፈላጊ ወጪ እንዳይወጣ ማለትም የሹፌሩን የውሎ አበልና የተሽከርካሪን በአግባቡ ለመጠቀም ለማስቻል ኃላፊዎቹ በተሰጣቸው ተሽከርካሪ እንዲተቀሙ የተደረገ ነው፡፡ ከዚህ ሌላ አንዳንድ ጊዜ ያሉት ተሽከርካሪዎች ለመስክ ስራ ወደ ክልሎች በሚሄዱበት ጊዜ በከተማ ውስጥ የሚሰሩትን ስራዎች የኃላፊዎችን መኪና ኪሎ መትሩን በመመዝገብ የተጠቀምነውን ነዳጅ በማስላት ተጨማሪ ነዳግ እየተሰጠ ስራዎች እንዲሰሩ ይደረጋል፡፡ ይህ ደግሞ እንደ ተቋም ካለው የተሽከርካሪ ውስንነትና የስራ ስፋት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ስለሆነም ካለው መመሪያ ጋር የሚጋጭ እንዳልሆነና መመሪያን ለመጣስ እንዳልሆነና ያሉትን ውስን ተሽከርካሪዎች በማብቃቃት የተቋሙን ተልዕኮ ለመፈጸም ተብሎ የተሰራ መሆኑ ይታወቅልን፡፡

5.4.3 ስጋት፣

- ሚኒስቴር መ/ቤቱ ገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር ያወጣን የቁጥጥር ስርዓት ተከትሉ ካልሰራ ነዳጁ(ንብረቱ) ላልታለመለት አላማ ሊውል እና የመንግስት ሀብት ያላግባብ ሊጠፋ ይችላል፡፡
- የውስጥ የቁጥጥር ስርዓቱን ደካ መሆኑን አመላካች ሲሆን እና ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለወጣው ህግና ደንብ እንደማይገዛ አመላካች ሊሆን ይችላል፡፡

5.4.4 የማሻሻያ ሀሳብ፣

- በኦዲት ወቅት የተሠጠው ምላሽ ከከተማ ውጪ ወደ ተለያዩ ክልሎችና ከተሞች ሲሔዱ ያለው እና ተጨማሪው ተለይቶ የተጠየቀ ጥያቄ ስለሆነ መመለስ ያለበት በዚሁ መሰረት ነበር፡፡ የሚኒስቴሮቹን በተመለከተ በፀሀፊዎችና በሹፌሮቹ ስለሆነ መውጣት ያለበት በዚያ አግባብ ሲሆን ለማንና ለማን እንደሆነም መግለጫ ስላለው በዚሁ መሰረት የሚረጋገጥ ነው፡፡
- ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የነዳጅ አጠቃቀሙን በደንቡ መሠረት ተፈጻሚ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ማንኛውም ሰራተኛ መስሪያ ቤቱን ሲለቅ ንብረት እንደሚመልሰው የበላይ አመራርም ሲዘዋወሩ የወሰዱትን ንብረት በመመለስ ከመስሪያ ቤቱ የሚያገኙትን ጥቅማ ጥቅምም ከተዛወሩ ጀምሮ መቆም አለበት፡፡ ለወደፊቱ እንደዚህ አይነት ስህተቶች እንዳይፈፀሙ የሥራ አመራሩ ህጎችን ማክበር ይኖርበታል፡፡

5.5.1 ግኝት፡- የመንግስት ንብረት ለግል ጥቅም ስለመጠቀም በተመለከተ፡-

ስለፌዴራል መንግሥት ከፍተኛ ኃላፊዎች ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም ስለመወሰን አንቀጽ 5 ጥቅማ ጥቅሞች ንዑስ አንቀጽ 1 "ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች ከደመወዝ በተጨማሪ የሚከተሉት ጥቅማ ጥቅም ያገኛሉ፤ መኖርያ ቤት፣ የታራንስፖርት አገልግሎት፤ የሕክምና አገልግሎት፤ የስልክ አገልግሎት፤ የዓመት ዕረፍትና ልዩ ልዩ ፈቃዶች፡" እንዲሁምአንቀጽ 7 የትራንስፖርት አገልግሎት ንፁስ አንቀጽ 1 " ከፍተኛ የመንግስ ኃላፊዎች በይዞታቸው ሥር ሆኖ የሚጠቀሙበት እንዳስፈላጊነቱ ለደህንነታቸው ጥበቃ ተስማሚ የሆነ አንድ መኪና እንዲሁም ለቤተሰቦቻቸው አገልግሎት የሚውል እንድ አውቶሞቢል ይመደብላቸዋል፡፡" የሚል ሲሆን ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ስንመለከት፡-

- ለክቡር ሚኒስትር መኖርያ ቤት ዴል ኮምፒተር ከነ አክሰሰሬው በሞዴል 22 ቁጥር 451995፣ ኢንተርኔት ብሮዳ ባንድ (WIFI)ቁጥር 95100043495፣ ዮፒኤስ በሞዴል 22 ቁጥር 906913፣ ጀነሬተር፣ 45 ኤንች ቴሊቪዥን እና የኮምፒተር ጠረጴዛ በሞዴል 22 ቁጥር 906932 ወጥቶ የተሰጠ መሆኑን፡-
- የሰሌዳ ቁጥር 4-24550 V8 ቶዮታ፣4-20348 ቶዮታ ያሪስ፣4-17249 ቶዮታ ያሪስ እና4-17551ቶዮታ ፕራዶ ለክብሩ ሚኒስቴር የተሰጡ መሆኑን በኦዲታችን ወቅት ለማረጋገጥ ችለናል፡፡

1.7.2 <u>በኦዲቱ ወቅት የተሰጠ ምላሽ፣</u>

ለክቡር ሚኒስትሩ ሹፌር ለአቶ ካሳሁን ገመቹ እና አንድ ቶዮታ ፕራዶ ኮድ 4-17551 አቶ ግርማ ዘሪሁን ተረክበው ለፑል ስራና ለአጃቢዎች ጧትና ማታ የሰርቪስ አገልግሎት እየሰጠ ያለ እንጂ አራት ተሽከርካሪዎች ለክቡር ሚኒስትሩ ተሰቷል ተብሎ የቀረበው መረጃ ስህተትና አግባቢነት የሌለው ነው፡፡

1.7.3 <u>ስጋት፣</u>

የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱን ንብረት ላልተለመለት አላማ ሊውልና ንብረት በቂ ጥበቃ ላያገኝና ለብልሹ አሰራር መንገድ ሊከፍትና የውስጥ ቁጥጥር ስርዓቱ ደካማ መሆኑ አመላካች ሊሆን ይችላል፡

1.7.3 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ለሚኒስቴሮች ንብረትም ሆነ ማንኛውም ንብረት ሲጠየቅ በፀሀፊዎቻቸውና በሹፌሮቻቸው እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በህጉ መሰረት ለሹፌር መኪና ይሰጥ የሚል መመሪያ የሌለ ስለሆነ ለአቶ ካሳሁን ገመቹ እና ለአቶ ግርማ ዘሪሁን የተሰጠ ከሆነ ከመመሪያው ውጭ የተሰጠው ተሽከርካሪ፣ እንዲሁም መመሪያው ከሚፈቅደው ውጪ በመኖርያ ቤት ያሉ ንብረቶች ወደ መስሪያ ቤቱ ተመላሽ እንዲደረግ፣ እንላለን መስሪያ ቤቱ በተቀመጠው መመሪያ ብቻ መስራት አለበት፡፡

5.5.1 <u>ግኝት፣በተቀናጀ የሂሳብ አያያዝ ስርአት ያልተመዘገበ፣</u>

በፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል አንድ አንቀጽ 9 ክፍያ ለመፈፀሙ በፊት ሊደረግ የሚገባው ጥንቃቄዎች ስር ንዑስ አንቀጽ 3 "ዕቃዉ ወደ መስሪያ ቤቱ ዕቃ መጋዘን ለመግባቱ የዕቃ ገቢ ደረሰኝ መቅረቡ ማረጋገጥ እንዳለበት ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከ2006 በጀት ዓመት ጀምሮ በተቀናጀ የሂሳብ አያያዝ ስርአት ሲስተም (IFMIS- integrated financial Management information system) ትግበራ ገብቶ በመስራት ላይ ያለ ቢሆንም የግዥና ንብረት ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ስር የሚገቡ ዕቃዎች ማለትም ንብረትን ወደ ሲስተም ማስገባት እና ንብረት ተገዝተው ወደ መስሪያ ቤቱ ሲገባ በማንዋል እና በሲስተም የሚመዘገብ በመሆኑ በ2009 በጀት ዓመት ከወሰድናቸው ናሙና ውስጥ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለገዛቸው ዕቃዎች ሞዴል19 በማንዋል እና በሲስተም የተቆረጡ በመሆኑ አንድ ወጥ የሆነ አሰራር እንደማይከተሉ እና የተቀናጀ የሂሳብ አያያዝ ስርአት ሲስተም ሙሉ ለሙሉ እንዳልተገበረ እና ንብረቶች ሲቀመጡ በቂ

ጥበቃ እንደሌላቸው ዝናብ ሲዘንብ ንብረት ክፍል እንደሚገባ በኦዲታችን ወቅት ለማረጋገጥ ችለናል፡፡ ዝርዝሩን ቀጥሎ ቀርቧል፡-

ተ.ቁ	የአቅራቢ የድርጅት ስም	ቀን	የደረሰኝ	የገንዘብ መጠን	የክፍያ ምክንያት
1	ዋውፕራይም ሀዉስሰርቪስ ኃ/የተ/የግ/ማ	26/03/09	10679	115,999.99	የቢሮ ፈርኒቸር ግዥ በሲስተም የተቆረጠ
2	መሪም መሀመድ የመኪን ጌጣጌጥ	06/07/09	11516	4,749.50	የመኪና ግጣጌጥ ግዥ በሞዴል 19 ያልተመዘገበ
3	ሀርዲምኃ/የተ/የግ/ ማህበር	30/02/09	10495	37,605.00	ለሚኒስቴር አማካሪ ላፕቶፕ ኮምፒዉተር ግዥ በማንዋል እና በሲስተም የተቆረጠ
4	አመሀመዝገቡ ስልክ ሞባይል ና መሰል ቀፎዎች	30/02/09	10503	29,900.00	ለሚኒስቴር አማካሪ i-pad ግዥ በሲስተም የተመዘገበ
5	Jupiter trading	07/07/09	11536	30,450.01	ፕሪንተር ግዥ- በማንዋል
		09/06/09	11269	6,350.00	ለክቡር አቶ አዳሙ አያና ተሽከር ካሬ ወንበርና የኮምፒተር ጠረጴዛ ወንበር በሞዴል 19 ያልተመዘገበ
6	ትራንቮ ኦትሬዲንግ	29/02/09	10459	20,700.00	ላፕቶፕ ፕሬንተር በማንዋል እና በሲስተም የተቆረጠ
ጠቅላላ ድምር ብር				245,754.50	

5.5.2 በኦዲቱ ወቅት የተሰጠ ምላሽ፣

መንግስት ማናኛውንም ንብረት ገቢና ወጪ መመዝገብ ያለበት Integrated Financial Management Information System) ብቻ መሆን እንዳለበት ያስቀምጣል፡፡ በዚሁ መሰረት እንደ ተቋማችን ሲስተሙን ተግባራዊ ማድረግ የተጀመረ ቢሆንም ባለው የሰው ሀይል እጥረትና የሲስተም መቆራረጥ ምክንያት በማኑዋልና በሲስተም ነበር ፡፡ ይሁን እንጂ በ2009 በጀት ዓመት የቋሚ ንብረት ገቢና ወጪ ምዝገባና የቁጥጥር ሥራ ይሰራ የነበረው ሙሉ ለሙሉ በሲስተም አልነበረም፡፡ ምክንያቱም ስራው ይከናወን የነበረው በቀድሞው አሰራር/ማንዋል እንዲሁም በIFMIS/ በሲስተም ጎን ለጎን ነው፡፡ ይህም የሆነው በንብረት አስተዳደር ቡድን ባለሞያዎች በአብዛኛው በ2009 ዓ.ም አጋማሽ ጀምሮ የተቀጠሩ በመሆኑ በሲስተም ላይ ስልጠና ያልነበራቸው በመሆናቸውና ነባሮቹ ባለሙያዎችም የንብረት ገቢና ወጪ ምዝገባውን ሙሉ ለሙሉ በሲስተም ለመስራት የአቅም ክፍተት ስላላቸው አዳዲሶቹ ባለሙያዎች ስልጠና ወስደው አቅም እስከሚፈጠር የንብረት ምዝገባውን በማንዋል

የመከታተልና የመቆጣጠር ሥራ ሲሰራ ቆዋቷል፡፡ከዚህም ሌላ ሲስተሙ አዲስ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የኔትወርክ መቆራረጥ ችግሮችም ነበሩ፡፡ በመሆኑም በቀጣይ በሲስተሙ ብቻ ለመጠቀም ባለሙያዎችን እንዲሰለጥኑ በማድረግ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሙያዊ ድጋፍ እንዲደረግ በመጠየቅ ወደ ስራ እንዲገባ እየጠደረገ ይገኛል፡፡ ነገር ግን የአላቂ ንብረት ገቢና ወጪ በሲስተም እየተሰራ ነው፡፡ ስለዚህ በቀጣይ የቋሚ ንብረት ገቢና ወጪ ምዝገባን በሲስተም እንዲሰራ ለማድረግ የክትትልና ቁጥጥር ስራ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

5.5.3 <u>ስጋት፤</u>

መስሪያ ቤቱ ወደ IFMIS ሲስተም ገብቶ በቀድሞ አሰራር በማንዋል መጠቀሙ ንብረቱ በትክክል ስለመመዝገቡ አጠራጣሬ ሊያደርገው እና በግለሰቦች እጅ ገብቶ ሊቀር ይችላል፡፡

5.5.4 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ወደ በIFMIS (integrated financial Management information system) እየተጠቀሙ ማንዋሉ በቀድሞ አሰራር መመዝረቡ ትክክለኛ ሆኔ አላገኘነውም፡፡ ንብረቶች ሲቆጠሮ ድግግሞሽ መኖሩ የቆጠራ ሰነዱን ከሲስተም ጋር ለማስታረቅ አስቸጋሬ ያደርገዋል፡፡ ከ2006 ጀምሮ ያሉትን ንብረቶች እንኳ ወደ ሲስተም ማስገባት ባይቻል ሲስተሙ ከተተገበረ ጀምሮ ያለውን በሲስተም አለመመዝገቡ ትክክለኛ አሰራር አይደለም፡፡ንብረት ክፍል በጣም ውድ የሆነየተቀናጀ የሲቪል ሰርቪስ መረጃ አያያዝ ስርዓት /ICMIS/ የፕሮጀክት ንብረቶች ለብልሽት ይዳረጋል፡፡ ስለዚህ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ትኩረት ሰጥቶ የማስተካከያ እርምት መውሰድ አለበት፡፡ ክፍሉ አሁንም የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡ የስራ አመራሩ ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

6. <u>ልዩ ልዩ፣</u>

6.1.1. <u>ግኝት፣</u>

የፌደራል መንግስት የፋይናንስ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 15 መሠረት የመንግስት መስሪያ ቤቶች በበጀት አደረጃጀት ሥርዓት መሠረት የተፈቀደላቸውን በጀት የወጣውን ወጪ ማሳየት እንዲቻል ተለይቶ በተሰጣቸው የበጀት መለያ መደቦች ተጠቅመው የሂሳብ እንቅስቃሴያቸውን መመዝገብ እንዳለባቸው ያዛል ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዚሁ መሰረት መሰራቱን ለማረጋገጥ ኦዲት በምናደረግበት ጊዜ በተቀናጀ የሂሳብ አያያዝ ስርአት ሲስተም

(IFMIS- integrated financial Management information system) ላይ ተመዝግቦ ቢገኝም በሰነድ ላይ ግን ምንም ማስረጃ ያልተያያዘለት ብር 50,763,898.57 መሆኑን አረጋግጠናል፡፡

6.1.2 በኦዲቱ ወቅት የተሰጠ ምላሽ፣

መልስ አልተሰጠም፡፡

6.1.3 ስጋት፣

በሲስተም የተመዘገበው ሰነድ ከነ ደጋፊ ሰነድ ማስረጃቸው ላይያያዝ እና መከፈል የሌለበት ገንዘብ ያለ አግባባብ ሊከፈል ይችላል፡፡

6.1.4 የማሻሻያ ሀሳብ፣

የተቀናጀ የሂሳብ አያያዝ ስርአት ሲስተም (IFMIS) የተካው የማንዋል ስራውን እስከሆነ ድረስ ተመዝግበው የተሰረዙም ሆነ ማስተካከያ የተወሰደባቸው የክፍያ ሰነዶች መያያዝ ነበረባቸው፡፡በሲስተም ውስጥ እንደ ወጪ ተመዝግቦ በሰነድ ያልተያያዘ ወጪ ሰነዱ መያያዝ አለበት።

6.2.1 ግኝት፣

በፌዴራል መንግሥት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003 መሰረት የመንግሥት መ/ቤቶች የተቋቋሙበትን ዓላማዎች ለማስፈጸም ዕቅዶችና የዕለት ተዕለ ተግባራት በማከናወን ሂደት የሚከሰቱ ችግሮችንና የተጋላጭነት ደረጃ ለመለየት የውስጥና የውጭ ኦዲተሮችንና ሌሎች የሚመለከታቸውን ባለሙያዎች በመጠቀም የስጋት ምንጮች ዳሰሳ ማካሄደ እንዳለባቸው ተመልክቷል፡፡ ይሁን እንጂ ሚኒስትር መስሪያ ቤቱ የስጋት ምንጮችን በመለየት የስጋት ተጋላጭነት ፍተሻ ያላደረገ መሆኑ በኦዲታችን ወቅት ለማወቅ ችለናል፡፡

6.2.2 በኦዲቱ ወቅት የተሰጠ ምላሽ፣

መ/ቤታችን በፌዴራል መንግስት የውስጥ ቁጥጥር ደረጃዎች መመሪያ ቁጥር 8/2003 መሠረት የተዘረዘሩትን ኃላፊነቶችን በክፍል ሦስት ሥር የተጠቀሱትን ማለትም፡-

1. የበላይ አመራር ኃላፊ ኃላፊነቶችን ከ1-6፣
2. የውስጥ ኦዲተሮችን ኃላፊነት፣
3. የሠራተኞችን ኃላፊነቶችን በሥራ ክፍል ደረጃ ተግባራዊ እንዲሆን አድርጓል፡፡ ክፍል አራትም የመ/ቤቱን ሥራ ባህሪ መሠረት በማድረግ የረጅምና የመካከለኛ ጊዜ ዕቅድ በሚዘጋጅበት ወቅት ለመ/ቤቱ ዓላማ ስጋት የሆኑ ጉዳዮችን ከነምንጮቻቸው በስፋትና

በጥልቀት በግምገማ ተለይተው መከለካያ ስልቶች ተነድፎ የእርምት እርምጃ እየተወሰደ ነው፡፡ለምሳሌ መ/ቤቱ በቂ ልምድና ትምህርት ያላቸው ባለሙያዎች እንዲኖሩ፤የሚያሰራ መዋቅርና አደረጃጀት እንዲኖርና በየጊዜው በጥናት እንዲሻሻሉ በማድረግ፤የአመለካከት ማነቆዎችና ኪራይ ሰብሰቢነት፤ በመ/ቤት ሆነ በአገር ደረጃ ለዓላማዉ ማሳካት ስጋት በመሆናቸው ተለይተው የማስፈጸሚያ ስልት ተነድፎ እየተሰራበት ነው፡፡ የሀብት አስተዳደርን በተመለከተ በየሩብ ዓመቱ የስጋት አካባቢዎች ተለይተው በውስጥ ኦዲት ኦዲት እንዲደረጉ ተደርጎ የእርምት እርምጃ እየተወሰደ ነው፡፡በቀጣይ በሰው ሀብት አመራር፤በሪፎርም፤በመልካም አስተዳደርና መንግስታዊ አገልግሎቶችን አሰጣጥና ሀብት አጠቃቀምን በተመለከተ ስጋት የሚሆኑትን ተለይተው የስጋት አስዳደር ስልት የሚዘረጋ ይሆናል፡፡

6.2.3 <u>ስጋት፣</u>

ሚኒስትር መስሪያ ቤቱ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማስፈፀም እንቅፋት የሆኑ ችግሮች በቅድሚያ በመለየት የዕለት ከዕለት ሥራዎች በሚያከናዎንበት ሊያጋጥሙ የሚችሉትን ስጋት በጊዜ ዕልባት ሳይሰጥበት ሊቀር እና ይህም ያለውን ውስን ሀብትን በትክክል ላይጠቀምበት ይችላል፡፡

6.2.4 <u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

የመንግስት መ/ቤቶች የውስጥ ቁጥጥር ስርዓቱ በየጊዜው ከሚኖሩ የተለያዩ ውስጣዊና ውጫዊ ለውጦች ጋር የተጣጣመ እንዲሆን በየጊዜው በመገምገም ከየወቅቱ ሁኔታ ጋር የተገኛዘበ የቁጥጥር ስርዓት መቅረፅ አለባቸው፡፡ ይህም መ/ቤቱ የተቋቋሙበትን ዓላማዎች ለማስፈጸም ዕቅዶችና ዝርዝር የዕለት ተዕለት ተግባራት በማከናወን ሂደት የሚከሰቱ ችግሮችና የተጋላጭነት ደረጃ በመለየት የመ/ቤቱን ባለሙያዎች በመጠቀም የስጋት ምንጮች ዳሰሳ በማካሄድ የጸደቀ የስጋት አስተዳደር ፖሊሲ ሊኖረው ይገባል፡፡

6.3.1 <u>የ2008 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች በተመለከተ፣</u>

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል በወጣ አዋጅ ቁጥር 982/08 አንቀጽ 17/3 መሰረት ተመርማሪ መሥሪያ ቤቶች ከፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተላኩ ሪፖርቶች በተገለፁ ግኝቶች ላይ ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ በተሰጡ የማሻሻያ ሃሣቦችና አስተያየቶች መሠረት ከ15 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ አለባቸው፡፡ የወሰዱትን እርምጃ እና ለመውሰድ ካልቻሉ ምክንያቱን

በመግለጽ ለፌዴራል ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት ከላይ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማሳወቅ አለባቸው፡፡ በዚሁ መሰረት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የ2008 በጀት ዓመት ኦዲት ሪፖርት በተሰጠው አስተያየት መሰረት የእርምት እርምጃ ለመውሰድ የጊዜ ገደብ ቢያስቀምጥም እስከ አሁን የወሰዳቸው መሻሻሎች አለመኖራቸውን በኦዲት ወቅት ለማወቅ ችለናል፡፡

6.3.2<u>በኦዲቱ ወቅት የተሰጠ ምላሽ</u>፣

መልስ አልተሰጠም፡፡

6.3.3 <u>ስጋት</u>፣

በኦዲት ሪፖርቱ ላይ እርምጃ ባለመወሰዱ ምክንያት ለቀጣዩም ጊዜ ኦዲተሩ የውስጥ ቁጥጥሩና የአሰራር ስርዓቱ ላይ አሜኔታ ሊያሳጣውና ሚኒስቴር መ/ቤቱ ተጨማሪ የስራ ክፍተት እንዲኖር ሊያደርግ ይችላል፡፡

6.3.4 <u>የማሻሻያሀሳብ</u>፣

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ዘንድ የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እንዲቀረፍ ብሎም ግልፅነትና ተጠያቂነት እንዲሰፍን የመ/ቤቱ ሥራ አመራር በኦዲት በሚሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሠረት የእርምት እርምጃ በመውሰድ የበኩሉን አስተዋፅኦ ሊያበረክት ይገባል፡፡

በመጨረሻም ለተደረገልን የስራ ትብብር እናመሰግናለን!!!